## ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ አፍሪካ ።

### ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዘር ፡ ከምን ፡ ትውልድ ፡ እንደሆኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ሕዝቦችም ፡ በውስጥዋ ፡ እንዳሉ ፡ የሚያሳይ ።

፩ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብና ፡ መንግሥት ፡ በዋናው ፡ ነገር ፡ በአራት ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ። ነገደ ፡ አሪት ፤ ነገደ ፡ ካም ፤ ወይም ፡ ነገደ ፡ ኩሳ ፤ ነገደ ፡ ሴም ፤ ወይም ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፤ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ ናቸው ።

፪ ፤ ይህን ፡ ስለ ፡ አሏነ ፡ የሕዝቡንና ፡ የመንግሥቱን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የሆነውን ፡ ዐይነተኛውን ፡ ክፍል ፡ መናገራችን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዝርዝሩ ፡ ግን ፡ በየዘመኑ ፡ ከእስያ ፡ እየፈለሱ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ሕዝቦች ፡ እጅግ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

፫ ፤ ከነዚህም ፡ ስማቸው ፡ የታወቁት ፡ በየወገናቸው ፡ በአምልኮ ፡ በቋንቋ ፤ በሥርዓትም ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ።

፬ ፤ ደግሞ ፡ ከምን ፡ ዘር ፡ እንደሆኑ ፡ የማይታወቁ ፡ በየጊዜው ፡ ገብተው ፡ ሲኖሩ ፡ በኋላ ፡ የመጡት ፡ አስለቅቀዋቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዳር ፡ ለዳር ፡ የሚኖሩ ፡ ጥቂቶች ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ ስማቸውና ፡ ነገዳቸው ፡ በጣም ፡ ያልታወቁ ፡ በመልካቸውና ፡ በግብራቸው ፡ የካምን ፡ ዘሮች ፤ የከነዓንን ፡ ልጆች ፡ የሚመስሉ ፡ ናቸው ።

፭ ፤ ፩ ፡ ነገደ ፡ አሪት ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ አስቀድመው ፡ በመጀመሪያ ፡ ከእስያ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡና ፡ አገሪቱን ፡ ይዘው ፡ የነበሩ ፡ ነገደ ፡ አሪት ፡ የተባሉት ፡ ናቸው ። የነዚህም ፡ አባት ፡ ከአዳም ፡ ልጆች ፡ አንዱ ፡ አሪ ፤ ወይም ፡ አራም ፡ የተባለው ፡ ነው ። እርሱ ፡ ከ፩ሺ ፡ ፶ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፪ሺ ፡ ፪፻፶፮ ዓመተ ፡ ዓለም ፤ ፩ሺ ፡ ፪፻፹፭ ፡ ዓመት ፡ ከነልጅ ፡ ልጆቹ ፡ ፳፩ ፡ ነገሥታት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነገሡ ። በመጨረሻው ፡ ንጉሣቸው ፡ በሶሊማን ፡ ታጊ ፡ ጊዜ ፡ በኖኅ ፡ ዘመን ፡ በጥፋት ፡ ውሃ ፡ ተደመሰሱ ፡ አለቁ ።

፮ ፤ እነዚህ ፡ ሕዝብ ፡ በማየ ፡ አይኅ ፡ ከጠፉ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ በቢሎን ፡ ግንብ ፡ መፍረስና ፡ በቋንቋ ፡ ተለያይተው ፡ እስከ ፡ ሰዎች ፡ መበታተን ፡ ድረስ ፡ ፭፻፴፩ ፡ ዓመት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ ምድርም ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ የሌለበት ፡ ባዶ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነገደ ፡ ካም ፡ መጡና ፡ ኢትዮጵያን ፡ ወረስዋት ።

፩ ፤ ጥያቄ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብና ፡ መንግሥት ፡ በዋናው ፡ ነገር ፡ በስንት ፡ ይከፈላል ፡ ? የነገዱን ፡ ስም ፡ ተናገር ።

፪ ፤ በየዘመኑ ፡ እየፈለሱ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡት ፡ ከየት ፡ ተነሥተው ፡ ነው ፡ ?

፫ ፤ በአምልኮ ፤ በቋንቋ ፤ በሥርዓት ፡ አንድ ፡ ናቸውን ፡ ?

፬ ፤ ደግሞ ፡ በየጊዜው ፡ እየፈለሱ ፡ የገቡት ፡ የማን ፡ ነገድ ፡ ይመስላሉ ፡ ?

፭ ፤ ከሁሉም ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡት ፡ ነገድ ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ?

፮ ፤ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በኋላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የወረስዋት ፡ ነገድ ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ነገደ ፡ ካም ።

፩ ፤ ካም ፡ ከእስያ ፡ በባብኤልመንደብ ፡ ተሻግሮ ፡ መጥቶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ገባ ። ይህም ፡ የሆነ ፡ በ፪ሺ፯፻፹፯ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ፪ሺ፯፻፲፫ ፡ ዓመት ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ነው ።

፪ ፤ ካም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፳፰ ፡ ዓመት ፡ ገዝቶ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ ሂዶ ፡ ሶርያንም ፡ እይዛለሁ ፡ ብሎ ፡ ከሴም ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ በጦር ፡ ሞተ ። ልጆቹ ፡ ግን ፡ ታላቅ ፡ ወንድማቸውን ፡ ኩሽን ፡ በላያቸው ፡ አንግሠው ፡ ኢትዮጵያን ፡ ወረሱ ። ነገደ ፡ ካም ፡ እስከ ፡ የልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ፳፭ ፡ ነገሥታት ፡ ከ፪ሺ፯፻፹፯ ፡ እስከ ፡ ፫ሺ ፡ ፭፻፲፭ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ፯፻፵፫ ፡ ዓመት ፡ ነግሠው ፤ ኢትዮጵያን ፡ ገዙ ።

### በነገደ ፡ ካም ፡ ወይም ፡ በነገደ ፡ ኩሳ ፡ መንግሥት ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ገቡ ፡ ሕዝብ ።

፫ ፤ በነዚህ ፡ በነገደ ፡ ኩሳ ፡ (ካም) ፡ መንግሥት ፡ ዘመን ፡ መኻከል ፡ ፫ ፡ ነገዶች ፡ በየጊዜው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገቡ ። እነርሱም ፡ ነገደ ፡ ሻንቅላ ፤ ነገደ ፡ ቅማንት ፡ ነገደ ፡ ወይጦ ፡ ናቸው ። ወንድማቸውም ፡ ሐማቲ ፡ ይባላል ። ሁሉም ፡ የከነዓን ፡ ልጆች ፡ ናቸው ። የነዚህም ፡ ነገድ ፡ አበቶች ፡ ሲኒ ፤ አርዋዲ ፤ ሳምሬ ፡ ናቸው ። ያ፬ኛው ፡ ወንድማቸው ፡ የሐማቲ ፡ ልጆች ፡ በኋላ ፡ በነገደ ፡ አግዓዝያን ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገቡ ። ሲኒ ፡ የሻንቅሎች ፤ አርዋዲ ፡ የቅማንቶች ፡ ሳምሬ ፡ የወይጦች ፤ ሐማቲ ፡ የሸናሾች ፡ አበቶች ፡ ናቸው ።

፬ ፤ የሲኒ ፡ ልጆች ፡ በእስያ ፡ ሲኖሩ ፡ መልካቸው ፡ እንደ ፡ እስያ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። በፊት ፡ ወደ ፡ አፍሪቃ ፡ ከመጡ ፡ ሻንቅሎች ፡ ጋር ፡ ቢቀላቀሉ ፡ በመጋባትም ፡ ባገሩ ፡ አየርም ፡ እንደ ፡ ሻንቅሎች ፡ ጥቍሮች ፡ ሆኑ ። በፊት ፡ በታችኛው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሱዳንና ፡ በኑቢያ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ወደ ፡ ደጋይቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወጡ ።

፭ ፤ እኒህ ፡ የሲኒ ፡ ልጆች ፡ ጥቍሮች ፡ የሆኑት ፡ ከሻንቅሎች ፡ ጋር ፡ በመቀላቀል ፡ ነው ። ከሲዮኒ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግሥት ፡ በነገሠች ፡ በ፫ኛው ፡ ዓመት ፡ በ፫ሺ ፡ ፷፱ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ በ፪ሺ ፡ ፬፻፴፩ ፡ ዓመት ፡ ከልደት ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገቡ ። ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ሁነው ፡ ወጡና ፡ ከብታቸውን ፡ ይዘው ፡ ከጭልጋ ፡ አፋፍ ፡ እስከ ፡ በሽሎ ፡ አፋፍ ፡ ሰፈሩ ። ሰፈሩ ፡ ስንል ፡ ቦታ ፡ እያዩ ፡ ተሰማሩ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከጭልጋ ፡ እስከ ፡ በሽሎ ፡ አፋፍ ፡ አንድነት ፡ ሰፈሩ ፡ ማለት ፡ አይደለም ።
እኒህም ፡ ሻንቅሎች ፡ ከብት ፡ ከመጠበቅና ፡ ሥጋና ፡ የዛፍ ፡ ፍሬ ፡ ከመብላት ፡ በቀር ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ እኽል ፡ መዝራት ፡ ሌላም ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ አያውቁም ፡ ነበሩ ። ዋሻ ፤ ታላቅ ፡ ደንጊያ ፡ ያገኙ ፡ ከዋሻ ፡ ከደንጊያ ፡ ተጠጉ ። ያላገኙ ፡ የቅጠል ፡ ጐጆ ፡ አድርገው ፡ ተቀመጡ ። ከብታቸውን ፡ ይዘው ፡ ሣር ፡ ወዳለበት ፡ እያዩ ፡ ሲሰፍሩና ፡ ሲያበሉ ፡ ሲዞሩ ፡ ይኖሩ ፡ ነበርና ፡ ለጊዜው ፡ ለነገደ ፡ ኩሳ ፡ መንግሥት ፡ ገበሩ ። ቀንበር ፡ ባከበዱባቸው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ብርቱ ፡ ጠብ ፡ ተጣሉና ፡ ጽኑ ፡ ውጊያ ፡

ተዋጉ ። ድል ፣ ሲያደርጉ ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜም ፣ ድል ፣ ሲሆኑ ፤ ሲታረቁ ፤ ሲሸፍ ቱም ፤ ሲገብሩ ፤ እምቢ ፣ ሲሉም ፣ የኋለኞች ፣ የኢትዮጵያ ፣ ሕዝብ ፣ አባቶች ፣ ነገደ ፣ ሴም ፣ (ነገደ ፣ ዮቅጣን ፣) አግዓዝያን ፤ ሻንቅሎችንም ፤ ነገደ ፣ ኩሳንም ፣ ሁሉ ንም ፣ አስለቅቀው ፣ ወደ ፣ ታችኛው ፣ የኢትዮጵያ ፣ ቆላ ፣ (በረሃ ፣) እስኪያሳድድ ዋቸው ፣ ድረስ ፣ ሻንቅሎች ፣ ፩፻፵፮ ፣ ዓመት ፣ በደጋዪቱ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ተቀመጡ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ካም ፣ ከእስያ ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የተሻገረው ፣ በየት ፣ ነው ፣ ?
፪ ፤ ካም ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ተመልሶ ፣ ወደ ፣ እስያ ፣ የተሻገረው ፣ ኢትዮጵያን ፣ ስንት ፣ ዓመት ፣ ከገዛ ፣ በኋላ ፣ ነው ፣ ?

የሞተበትን ፣ ምክንያት ፣ ተናገር ።

፫ ፤ በነገደ ፣ ኩሳ ፣ መንግሥት ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የገቡትን ፣ ነገድ ፣ ተናገር ።
፬ ፤ የሲኒ ፣ ልጆች ፣ ጥቍር ፣ የሆኑት ፣ በምን ፣ ምክንያት ፣ ነው ፣ ?
፭ ፤ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የገቡት ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ?
፮ ፤ የነዚህን ፣ የሻንቅሎች ፣ አኗኗር ፣ ገልጸህ ፣ ተናገር ።

## ምዕራፍ ፣ ፺፫ ።

### ነገደ ፣ ቅማንት ።

፩ ፤ ሐር ፣ በነገሠ ፣ በ፲፫ ፣ ዓመት ፣ በ፫ሺ ፣ ፺ ፣ ዓመተ ፣ ዓለም ፣ ፪ሺ ፣ ፬፻፲ ፣ ከልደት ፣ በፊት ፣ የአርዋዲ ፣ ልጅ ፣ የከነዓን ፣ የልጁ ፣ ልጅ ፣ የቅማንቶች ፣ አባት ፣ አይነር ፣ ከከነዓን ፣ አገር ፣ ተሰዶ ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ገባ ። የከነዓን ፣ ልጅ ፣ አርዋዲ ፣ ፺ ፣ ወለደ ፣ ከ፺ቱ ፣ አንዱ ፣ አይነር ፣ የተባለው ፣ ሚስቱን ፣ እንተላን ፣ ይዞ ፣ ከወንድሞቹ ፣ ተለይቶ ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ወጣ ፤ ፺ቱ ፣ ወንድሞቹ ፣ ግን ፣ በእስያና ፣ በምድረ ፣ ግብዕ ፣ ተበታትነው ፣ ቀሩ ። ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የወጣው ፣ አይነር ፣ በምድረ ፣ እስያ ፣ በከነዓን ፣ አገር ፣ ረኃብ ፣ በጸና ፣ ጊዜ ፣ ከወንድሞቹና ፣ ከወገኖቹ ፣ ተለይቶ ፣ ሚስቱን ፣ እንተላን ፣ ይዞ ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ወጥቶ ፣ ሰው ፣ ሳያየውና ፣ ሳያውቀው ፣ በከርከር ፣ ዱር ፣ በረሃ ፣ አውሬ ፣ አድኖ ፤ የዛፍ ፣ ፍሬ ፣ ለቅሞ ፣ እየበላ ፣ ብዙ ፣ ዘመን ፣ ተቀመጠ ። ሰው ፣ ሳያየውና ፣ ሳያውቀው ፣ ብዙ ፣ ዘመን ፣ ስለ ፣ ተቀመጠ ፤ የቅማንቶችን ፣ አባት ፣ ዕንጨት ፣ ወለደው ፣ የዕንጨት ፣ ፍሬ ፣ ነው ፤ ከዕጨት ፣ የተገኘ ፣ ነው ፣ የሚሉ ፣ አሉ ። ነገር ፣ ግን ፣ በዚህ ፣ ነገራቸው ፣ ከንቱ ፣ የሐሰት ፣ ተረትን ፣ ያጫውታሉ ፣ እንጂ ፣ የውነት ፣ ነገር ፣ አይደለም ። የሰው ፣ ሁሉ ፣ ምንጭና ፣ አባት ፣ አዳም ፣ እን ደሆነ ፣ መጽሐፍ ፣ ቅዱስ ፣ ይነግረናል ። ጥቂት ፣ ተማርን ፤ መጽሐፍ ፣ መረመርን ፣ የሚሉ ፣ ግን ፣ ስለ ፣ ቅማንቶች  ትውልድ ፣ ሲተረኩ ፣ እንዲህ ፣ ይላሉ ። በኢያሱ ፣ ወልደ ፣ ነዌ ፣ ዘመን ፣ ኢያሱንና ፣ የእስራኤልን ፣ አለቆች ፣ በቅርብ ፣ ሳሉ ፣ የሩቅ ፣ መስለው ፣ አታልለው ፣ ያስማልዋቸው ፣ ሰብአ ፣ ገባዖን ፣ በእስራኤል ፣ ርስት ፣ መኻ ከል ፣ ነበሩና ፣ መሐላ ፣ እንዳይፈርስባቸው ፣ ሳያጠፉዋቸው ፣ ለሕዝቡ ፣ ሣር ፣ አጫጅ ፤ ዕንጨት ፣ ለቃሚ ፣ አደረጉዋቸው ። ለልጅ ፣ ልጅ ፣ የእስራኤል ፣ ዜጎች ፣ ሆኑ ።

ኢ.ያሱ ፣ ፱፡፫—፳፯ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፣ በሰሎሞን ፡ ጊዜ ፣ ቀዳማዊ ፣ ምኒልክ ፣ ወደ፣
ኢ.ትዮጵያ ፣ ሲመጣ ፡ አብረው ፣ የመጡ ፣ ናቸው ። በጥንተ ፣ ግብራቸው ፣ ንጉሥ፣
በሚኖርበት ፣ ከተማ፣በዜግነት ፣ ማር፣እያጨዱ ፤ ዕንጨት፣እየለቀሙ ፣ ኖሩ፣ሲሉ ፣
ይተርካሉ ፤ በጎንደር ፣ ዙሪያ፣ዜጎች ፣ ሁነው ፣ ተሠሩ ፣ ይላሉ ። ይህንንም ፣ በአፍ፣
ብቻ ፤ ይተርካሉ ፣ እንጂ፣የተጻፈ ፣ ቁም ፣ ነገር ፣ ታሪክ ፣ የላቸውም ።

፪ ፤ እኒህ ፣ ቅማንቶች ፣ በአምልኮት ፤ በቋንቋ ፤ በወገን ፤ የተለዩ ፣ አረማያውን ፣ ሕዝብ ፣
ናቸው ። ከቀዳማዊ፣ምኒልክ፣እስከ ፣ አጼ፣ፋሲል፣መንግሥት፣፬ሺ፡፯፻፸፱፡ዓመት ፣
ነው ። ጎንደር ፣ ከተሠራ ፣ ፬፻፺፰ ፣ ዓመት ፣ ነው ። የቅማንቶች ፣ መኖሪያ ፣ በከር
ከር ፣ በጭልጋ ፤ በጋላ፣ አገር ፣ በቦባ ፤ በኮሶጌ ፤ በጆኒ ፣ ፈንቀራ ፣ በዙሪያቸውም ፣
ባሉ ፣ አገሮች ፣ ነው ።

፫ ፤ እኛ ፣ ግን ፣ እነዚህን ፣ አሁን ፣ የተቈጠሩትን ፣ የቅማንት ፣ አገሮች ፣ ጥንት ፣ ከመ
ሠረት ፣ አገራቸው ፣ እንደ ፣ ነበረ ፣ በኋላ ፣ ግን ፣ በዘመነ ፣ ክርስትና ፣ የክርስቲያን ፣
ነገሥታት ፣ ቅማንትን ፣ የክርስቲያን ፣ ዜጋ ፣ አድርገው ፣ በላያቸው ፣ ሥሬ ፣ እንደ፣
ሠሩባቸው ፣ በአገራቸውም ፣ መኻከል ፣ ጕልተኛ ፣ ሆኖ ፣ ክርስቲያን ፣ እንደ ፣ ገባ
ባቸው ፤ በአገራቸውም ፣ ሁሉ ፣ አብያተ ፣ ክርስቲያናት ፣ እንደ ፣ ተሠሩባቸው ፣
እናውቃለንና ፣ ብዙዎች ፣ ታሪክ ፣ ጸሐፊዎች ፣ እንደሚሉ ፣ የቅማንቶች ፣ አባት ፣
አይነር ፣ በፊት፣እንደ፣መጣ ፣ አገርንም ፣ ይዞ፣እንደ፣ነበረ ፣ ነገራችንን ፣ በዚህ፣ እና
ጸናለን ።

፬ ፤ አይነር ፣ ከሚስቱ፣ከእንተላ ፣ ፱ ፣ ወንዶች ፣ ፫፣ሴቶች ፣ወለደ ፤ ስማቸውም ፣ እኒህ ፣
ናቸው ። ክብርዋ ፤ አይደረኪ. ፤ እንግሢ ፤ ነዚ ፤ ይዞና ፤ በአቲ ፤ ዳዮን ፤ ሸመኒ ፤
ከደሴቲ ። የሴቶቹ ፣ ስም ፣ ይህ ፣ ነው ። ውሸን ፤ እቲቱ ፤ ፍርዳቀን ፤ኒማልጊን፤
ይባዕስ ፤ እኒህ ፣ ፫ቱ ፣ ሁሉ ፣ ባል ፣ ሳያገቡ ፣ በድንግልና ፣ ሞቱ ፣ ይባላል ። ይባ
ዕስ ፣ ከሁሉ ፣ የበለጠች ፣ ታላቅ ፣ ሰው ፣ ነበረች ፣ ይላሉ ።

፭ ፤ የክብርዋ ፣ መኖሪያ ፡ በጆኒ ፣ ፈንቀራ ፤ ሰራክ ፤ ሰገር ፣ በሚሉት ፣ አገር ፣ ነው ።
አይደረኪ. ፣ መኖሪያው ፣ በከርከር ፣ ነው ። አይደረኪ.ን ፣ ቅማንቶች ፣ አከበርነው ፣
ብለው ፣ አባት ፣ እናት ፣ የለውም ፤ ከሰማይ ፣ የወረደ ፣ ነው ፣ ይሉታል ። ነገር ፣
ግን ፣ ይህ ፣ ተረት ፣ ይቅርና ፣ ያለ ፣ ጥርጥር ፣ የአይነር ፣ ልጅ ፣ ነው ።

፮ ፤ እንግሢ ፤ ነዚ ፤ ይዞና ፤ ሸመኒ ፤ ከደሴቲ ፤ የከርከር ፣ ቅማንቶች ፣ አባቶች ፣
ናቸው ። ዳዮን ፣ የጭልጋ ፣ ቅማንቶች ፣ አባት ፣ ነው ። በአቲ ፣ የጋላ ፣ አገር ፣
ቅማንቶች ፣ አባት ፣ ነው ።

፯ ፤ አንባቢ. ፣ ሆይ ፤ የጋላ ፣ አገር ፣ ማለት ፣ ጋላ ፣ ቤት ፣ ሁሉ ፣ አይመስልህ ።
በጭልጋና ፣ በጋባ ፣ አጠገብ ፣ ያለ ፣ አገር ፣ ነው ። ትንክበሊ. ፣ የበአቲ ፣
ልጅ ፤ በጋባ ፣ የሚኖሩ ፣ ቅማንቶች ፣ አባት ፣ ነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የቅማንቶች ፡ አባት ፡ አይነር ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገባው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
፪ ፤ የቅማንቶች ፡ መኖሪያ ፡ አገሮች ፡ ማን ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ?
፫ ፤ አይነር ፡ ስንት ፡ ልጆች ፡ ወለደ ፡ ? ስማቸውን ፡ ዘርዝረህ ፡ ተናገር ፡ ?
፬ ፤ ቅማንቶች ፡ የሚያከብሩት ፡ ማንን ፡ ነው ፡ ?
፭ ፤ የጋላ ፡ አገር ፡ ማለት ፡ የትኛው ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፴፯ ።

### ነገደ ፡ ወይጦ ።

፩ ፤ ከኩሳ ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ሳባ ፡ ፩ኛ ፡ የተባለው ፡ በነገሠ ፡ ባ፲፭ ፡ ዓመት ፡ በ፫ሺ ፡ ፲፱ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ፪ሺ ፡ ፫፻፰ ፡ ዓመት ፡ ከልደት ፡ በፊት ፡ ነገደ ፡ ወይጦ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገቡ ። ስማቸው ፡ በአባታቸው ፡ ስም ፡ ዋቶ ፡ ነው ። ከዋቶ ፡ እያደረ ፡ ወደ ፡ ወይጦ ፡ ተመለሰ ። ሰምሪ ፡ ዋቶን ፡ ወለደ ፤ ዋቶ ፡ የወይጦች ፡ አባት ፡ ነው ።
፪ ፤ መጀመሪያ ፡ በ፫ሺ ፡ ፲፱ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ በምስርና ፡ በሱዳን ፡ አገር ፡ ብርቱ ፡ ረኃብ ፡ ሆነ ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የዋቶ ፡ ነገድ ፡ ወይጦች ፡ በዐባይ ፡ ወንዝ ፡ ለወንዝ ፡ እየሄዱ ፤ አዞውን ፤ ጉማሬውን ፤ ይብራውን ፤ ጋጋኖውን ፤ ሌሎችንም ፡ አዕዋፍ ፡ ዓሣውንም ፡ እየበሉ ፡ እስከ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወጡ ። ተከፍለው ፡ በጣና ፡ ባሕር ፡ ዙሪያ ፡ ተቀመጡ ። ተከፍለው ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ከፋ ፡ ሄዱ ። በጋላ ፡ አገርም ፡ ተቀመጡ ። በጋላ ፡ አገርና ፡ በከፋ ፡ ያሉት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ባባታቸው ፡ በዋቶ ፡ ስም ፡ ዋቶ ፡ ወይም ፡ ዋታ ፡ ይባላሉ ። በጣና ፡ ባሕር ፡ ዙሪያ ፡ ያሉ ፡ ግን ፡ በዘመን ፡ ብዛት ፡ ዋቶ ፡ ተለውጦ ፡ ወይጦ ፡ ተባሉ ። ዳግመኛ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፤ ወይም ፡ ነገደ ፡ አግዓዝያን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ከሌላው ፡ ሕዝብ ፡ ተለይተው ፡ በአምልኮ ፡ የማይቀላቀሉ ፡ ያገኙትንም ፡ እንስሳ ፡ ርኩስና ፡ ቅዱስ ፡ ሳይለዩ ፡ ሁሉን ፡ የሚበሉ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አይተው ፡ እኒህ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ። ዋቶ ፡ ይባላሉ ፤ ያገኙትንም ፡ ሁሉ ፡ ይበላሉ ፡ አልዋቸው ። ነገደ ፡ አግዓዝያንም ፡ የኒህስ ፡ ስማቸው ፡ ዋቶ ፡ አይደለም ፡ ያገኙትን ፡ ሁሉ ፡ የሚበሉ ፡ የማይጸየፉ ፡ ናቸውና ፡ ስማቸው ፡ ውሂጦ ፡ ነው ፡ አሉ ። ስለዚህም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ውሂጦ ፡ ተባሉ ፤ ውሂጦ ፡ ማለትም ፡ ዋጮ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከዘመን ፡ ብዛት ፡ ግን ፡ እያደረ ፡ ውሂጦ ፡ ተለውጦ ፡ ወይጦ ፡ ተባለ ፡ ይላሉ ። በፊት ፡ እንዳልነ ፡ ወይጦ ፡ የተባሉ ፡ በጣና ፡ ባሕር ፡ ዙሪያ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። በጋላና ፡ በከፋ ፡ ያሉ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ዋታ ፡ ይባላሉ ።
፫ ፤ ሁለተኛ ፡ በምስርና ፡ በሱዳን ፡ አገር ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተከፍለው ፡ ቀርተው ፡ የነበሩ ፡ ወይጦች ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ደግሞ ፡ ከሥጋዌ ፡ በኋላ ፡ በ፺፻፵ ፡ ዓመት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ለትም ፡ በነገሠ ፡ ባ፲ ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጡና ፡ በጣና ፡

ባሕር ፡ ዙሪያ ፡ ከሚኖሩ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ጋር ፡ ተቀላቀሉ ። ከነሱም ፡ የእስላሞችን ፡ ነቢይ ፡ የሙሐመድን ፡ ወሬ ፡ ሰምተው ፡ ሙሐመድ ፡ የአላህ ፡ ነቢይ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ተቀብሉና ፡ አመኑ ፤ ስለዚህ ፡ እንዴት ፡ ዋላችሁ ፡ ሲልዋቸው ፡ አልሐምዲላ ፡ ይላሉ ፤ ሙስሐባም ፡ በአንገታቸው ፡ ያስራሉ ፤ ቊርዓንን ፡ ግን ፡ አይቀበሉምና ፡ እንደ ፡ እስላም ፡ ሰጊድ ፡ ጾምና ፡ ጸሎትም ፡ አያውቁም ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ነገደ ፡ ወይጦ ፡ ወደ ፡ ኢ.ትዮጵያ ፡ የገቡት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
፪ ፤ የዋታዎች ፡ (ወይጦ)መኖሪያ ፡ በየት ፡ ነው ፡ ?ስለነሱ ፡ ዘርዝረህ ፡ ተናገር ።
፫ ፤ ሃይማኖታቸው ፡ ምንድነው ፡ ?

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፵፯ ።

### ነገደ ሽናሽ ።

የሽናሽ ፡ መጀመሪያ ፡ አባታቸው ፡ ሐማቲ ፡ ነው ። ሐማቲ ፡ ጉማን ፡ ዠገትን ፡ ጎንጋን ፤ ዱራን ፡ ወለደ ፤ እኒህም ፡ አራቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ የሽናሾች ፡ አባቶች ፤ በዘመነ ፡ አግዓዝያን ፡ አይባ ፡ ሁለተኛ ፡ ስሙ ፡ ሰቢ ፡ ፪ኛ ፡ የተባለ ፡ በነገሠ ፡ በ፳፱፻ ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ኢ.ትዮጵያ ፡ ገቡ ፡ ይህም ፡ የሆነ ፡ በ፫ሺ ፡ ፯፻፷፱ ፡ ዓመት ፡ ዓለም ፡ ከልደት ፡ በፊት ፡ ፩ሺ ፡ ፰፩ ፡ ዓመት ፡ ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ ምስር ፡ በገባበት ፡ ዘመን ፡ ነው ።

፪ ፤ እኒህ ፡ የነገደ ፡ ሽናሽ ፡ አባቶች ፡ ከምድረ ፡ ከነዓን ፡ ርስትን ፡ ባጡ ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ ተሰደው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ግብፅ ፡ ገቡ ። በምድረ ፡ ግብፅም ፡ እጅግ ፡ ሀብታሞች ፡ ሆኑ ፤ የግብፃችንም ፡ ጥበብ ፡ የአስማትንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተማሩ ። ይህ ፡ ሳይቀር ፡ በዚያ ፡ አንድ ፡ ቃዳ ፡ የሚሆን ፡ መሬት ፡ አልነበራቸውምና ፡ ለከብታቸው ፡ ማሰማሪያ ፡ ስፍራ ፡ አጡ ፤ አርሰው ፤ ዘርተው ፤ እኽል ፡ አምርተው ፡ የሚበሉበት ፡ መሬት ፡ ስላጡ ፡ በግብፅ ፡ ሰዎችና ፡ በነሱ ፡ መኻከል ፡ ሁልጊዜ ፡ ፀብና ፡ ክርክር ፡ ሁከትም ፡ ሆነ ። ስለዚህ ፡ ነገደ ፡ ሽናሽ በጠብና ፡ በረኃብ ፡ ምክንያት ፡ ከምድረ ፡ ግብፅ ፡ ተሰደው ፡ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ሆነው ፡ በዐባይ ፡ ወንዝ ፡ ለወንዝ ፡ ወጥተው ፡ በዳሞትና ፡ በኵታይ ፤ ባሞሩ ፡ መኻከል ፡ በዐባይ ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ማዶ ፡ ሰፈሩና ፡ ከደጋው ፡ ኢ.ትዮጵያ ፡ ተሰዶ ፡ በዐባይ ፡ ወንዝ ፡ ለወንዝ ፤ ከቈላው ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረውን ፡ ሻንቅላ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ አደረጉትና ፡ አጠፉት ፤ አገሩንም ፡ ያዙት ። ከሞት ፡ የተረፈውን ፡ ሻንቅላ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ባርያ ፡ አድርገው ፡ ገዙት ። አገሩንም ፡ አራቱ ፡ ነገድ ፡ ተካፍለው ፡ በየአባታቸው ፡ ስም ፡ ጠሩት ። የጉማ ፡ ልጆች ፡ የደረሳቸውን ፡ አገር ፡ በአባታቸው ፡ ስም ፡ ጉማ ፡ አሉት ። የዠገት ፡ ልጆችም ፡ በአባታቸው ፡ ስም ፡ ዠገት ፡ አሉት ። የጎንጋ ፡ ልጆችም ፡ በአባታቸው ፡ ስም ፡ ጎንጋ ፡ አሉት ። በአ

ገው ፡ ምድርና ፡ በነሱ ፡ መለያያ ፡ ባለው ፡ ታላቅ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ያሉ ፡ የዱራ ፡ ልጆችም ፤ ወንዙን ፡ በአባታቸው ፡ ስም ፡ ዱራ ፡ አሉት ። ይህም ፡ ዱራ ፡ የተ ባለ ፡ ወንዝ ፤ የአገው ፡ ምድርና ፡ የሽናሽ ፡ የሻንቅላ ፡ መለያያ ፡ ነው ።

፫ ፡ ሽናሾች ፡ ቀድሞ ፡ በየነገዳቸው ፡ የተማ ፡ ልጆች ፡ ተማ ፤ የዥገት ፡ ልጆች ፡ ዥገት ፡ የጎንጋ ፡ ልጆች ፡ ጎንጋ ፤ የዱራ ፡ ልጆች ፡ ዱራ ፡ ይባሉ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሽናሽ ፡ ወይም ፡ ሽናሻ ፡ የሚባል ፡ የጥቅል ፡ ስም ፡ አልነበራቸውም ። አሁን ፡ በቅርቡ ፡ የአማራ ፡ ሕዝብና ፡ ቋንቋ ፡ ከሠለጠነ ፡ ወዲህ ፡ እጅግ ፡ በዝተው ፡ ቀድሞ ፡ ሻንቅላን ፡ አጥፍተውና ፡ አጥቅተው ፡ የያዙት ፡ አገር ፡ አልበቃቸው ፡ ብሎ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወጥተው ፡ አገውንና ፡ ዳሞትን ፡ እየወጉ ፡ ይዘርፉ ፡ ስለ ነበረ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጩኸትና ፡ ሽብር ፡ ሆነ ። ምን ፡ ጩኸትና ፡ ሽብር ፡ ነው ፡ ? ብለው ፡ የዳሞት ፡ ሰዎች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ቢጠያየቁ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ሽናሺ ፡ የሆነ ፡ ሕዝብ ፡ ለጦርነትና ፡ ለዘረፋ ፡ መጣብን ፡ አሉ ። ስለዚህ ፡ እነዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ሽናሽ ፡ ተባሉ ፡ ሽናሽ ፡ ማለትም ፡ በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፬ ፤ ሽናሾች ፡ አረማውያን ፡ ናቸው ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ በዳሞት ፡ ደንበር ፡ በጉሙር ፡ አጠ ገብ ፡ በማቢቢል ፤ በኮሴ ፡ ያሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ከሆኑ ፡ ብዙ ፡ ጊዜያቸው ፡ ነው ። ከዱራ ፡ ወዲያ ፡ ማዶና ፡ ፀዐባይ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አረማውያን ፡ ናቸው ። አምልኮአቸውም ፡ እንደ ፡ ጋላ ፡ በወፍ ፤ በአሞራ ፤ በዛፍ ፤ በደንጊያ ፤ በዛጐል ፡ መጣል ፤ በሙዋርተኝነት ፡ ነው ፤ የቀድሞ ፡ አባቶቻቸው ፡ ከምድረ ፡ ግብፅ ፡ አስማተኞች ፡ እንደ ፡ ተማሩ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ብዙ ፡ አስማተኞችና ፡ ባለመድኃ ኒተኞች ፡ አሉ ፤ ጽሕፈት ፡ ግን ፡ አያውቁም ፡ መጽሐፍ ፡ የላቸውም ።

## ጥያቄ ፤

፩ ፤ የሽናሾች ፡ አባቶች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
፪ ፡ ነገደ ፡ ሽናሽ ፡ የመጡት ፡ ከወዴት ፡ ነው ፡ ?
፫ ፤ ሽናሽ ፡ በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ?
፬ ፤ ነገደ ፡ ሽናሽ ፡ የሚያመልኩት ፡ በምንድነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

### ነገደ ፡ ዮቅጣን ።

፩ ፤ እኒህ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ የሴም ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ። ሴም ፡ ፲፭ ፡ ልጆች ፡ ወለደ ። ከ፲፭ቱ ፡ ፫ኛው ፡ አርፋክሳድ ፡ ነው ። አርፋክሳድ ፡ ቃይናንን ፡ ወለደ ። ቃይ ናን ፡ ሳላን ፡ ወለደ ። ሳላ ፡ ዔቦርን ፡ ወለደ ። ዔቦር ፡ ፋሌክንና ፡ ዮቅጣንን ፡ ወለደ ። ዮቅጣን ፡ በግእዝ ፡ ዮቃጢን ፡ ባማርኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ዮቅጣን ፡ በወዲያ ፡ አገር ፡ መጽሐፍ ፡ ዮሕጣን ፡ የካታን ፡ ይባላል ። ዮቅጣን ፡ ፲፫ ፡ ልጆች ፡ ወለደ ፡ ስማ

ቸውም ፣ አልሞዳድ ፤ ሳልፍ ፤ ሀስረሞት ፤ ያራህ ፤ ሀዶራም ፤ አውዛል ፣ ዶቅላ ፤ ሁባል ፤ ወይም ፣ ኑባል ፣ አቢማኤል ፤ ሳባ ፤ አውፌር ፤ ሀዊላ ፤ ዮባብ ፣ ናቸው ። ዘፍጥ ፲ ፣ ፳፮—፳፱ ፣ ስፍራውም ፣ በእስያ ፣ ምድር ፣ ከሜሻ ፣ እስከ ፣ ሠፋር ፣ እስከ ፣ ምሥራቅ ፣ ተራራ ፣ ድረስ ፣ ነው ። ዘፍ ፣ ፲ ፣ ፴ ።

፪ ፤ ከነዚህ ፣ ከ፲፫ቱ ፣ የዮቅጣን ፣ ልጆች ፣ ፫ቱ ፣ ሳባ ፤ አውፌር ፤ ሀዊላ ፤ አባል ፣ አቢማኤል ፤ በታ ፣ ባነሳቸው ፣ ስፍራ ፣ በጠበባቸው ፣ ጊዜ ፣ ከእስያ ፣ ተነሥተው ፣ ብዙ ፣ ሠራዊት ፣ ሁነው ፣ ሲፈልሱ ፣ ሲሄዱ ፣ ሲጓዙ ፣ የመን ፣ ደረሱ ፣ እኒሁ ፣ የሴም ፣ ዘር ፣ ነገደ ፣ ዮቅጣን ፣ ወደ ፣ የመን ፣ በገቡ ፣ ጊዜ ፣ ምንም ፣ በፖለቲካ ፣ ምክር ፣ ባይስማሙ ፣ ለኩሳ ፣ የመን ፣ ይገብሩ ፣ ነበር ። በኋላ ፣ ግን ፣ የኩሳ ፣ የመንን ፣ ደካምነት ፣ አይተው ፣ በተንኰልና ፣ በሌላም ፣ ጥበብ ፣ እርስ ፣ በርሱ ፣ አሸፍተው ፣ ከወገናቸው ፣ ያሮባ ፣ የተባለውን ፣ ብልሀተኛ ፣ ጀግና ፣ አንግሠው ፣ ለየመን ፣ ሁሉ ፣ ባለቤቶች ፣ ሆኑ ። እነዚሁ ፣ ነገድ ፣ በነገደ ፣ ካም ፣ መንግሥት ፣ መጨረሻ ፣ ጲአሪ ፣ ፩ኛ ፣ በነገሠ ፣ በ፲ ፣ ዓመት ፣ በ፫ሺ ፣ ፭፻፲ ፣ ዓመተ ፣ ዓለም ፣ በሺ ፣ ፱፻፺ ፣ ዓመት ፣ ከልደት ፣ በፊት ፣ አግዓዝያን ፣ ተባሉ ። ከነገደ ፣ ሴም ፣ ነገደ ፣ ዮቅጣን ፣ ከየመን ፣ ተነሥተው ፣ ብዙ ፣ ሠራዊት ፣ ሆነው ፣ በባብአል ፣ መንደብ ፣ ተሻግረው ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ገቡ ።

፫ ፤ በዚያን ፣ ዘመን ፣ ነገደ ፣ ዮቅጣን ፣ በየጊዜው ፣ በ፰ ፣ ስም ፣ ይጠሩ ፣ ነበር ። ሳቦች ፣ በደዎች ፤ አረኖች ፣ ትግሬዮች ፤ አግዓዝያን ፣ ይባሉ ፣ ነበር ።

፬ ፣ ኢትዮጲስ ፣ ሁለተኛ ፣ ሳባ ፣ የተባለው ፣ የአክሁናስ ፣ የልጁ ፣ ልጅ ፣ የቡልቃያ ፣ ልጅ ፣ ነው ። እናቱም ፣ የቱች ፣ ንጉሥ ፣ ልጅ ፣ ነች ። አግለዔ ፣ ትባላለች ። ኢትዮጲስ ፣ ፩ኛ ፣ ከ፫ሺ ፣ ፮፻፵፬—፫ሺ ፣ ፯፻ ፣ ዓመተ ፣ ዓለም ፣ ከሺ ፣ ፰፻፶፮—ሺ ፣ ፰፻ ፣ ዓመት ፣ ከልደት ፣ በፊት ፣ ፶፮ ፣ ዓመት ፣ ነገሠ ። አገሩም ፣ በስሙ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ተባለ ።

፭ ፤ ኢትዮጲስ ፣ ፩ኛ ፣ ከሞተ ፣ በኋላ ፣ በመንግሥቱ ፣ ልጁ ፣ ላክንዱን ፣ ሁለተኛ ፣ ስሙ ፣ ኖወርአሪ ፣ የተባለው ፣ ተተካ ።

፮ ፤ የኢትዮጲስ ፣ ፩ኛ ፣ ልጆች ፣ ፭ ፣ ናቸው ። እነርሱም ፣ ላክንዱን ፤ ሳባ ፤ ኖባ ፤ በለው ፣ ከለው ፣ ናቸው ። የመጀመሪያ ፣ ልጁ ፣ ላክንዱን ፣ መንግሥትን ፣ ወረሰ ። ፬ቱ ፣ ግን ፣ የአገር ፣ ርስትን ፣ ተካፍለው ፣ ያዙ ። ሰባ ፣ አሁን ፣ ትግሬ ፣ ተብሎ ፣ በሚጠራው ፣ አገር ፣ የተቀመጡ ፣ ሕዝብ ፣ አባት ፣ ነው ። አገሩም ፣ በሱ ፣ ስም ፣ ሳባ ፣ ተብሎ ፣ ይጠራ ፣ ነበር ። የመንግሥት ፣ መቧቀያና ፣ ግንዱ ፣ ይህ ፣ ነው ። የሚሉ ፣ አሉ ።

ነገር ፣ ግን ፣ በስም ፣ ሞክሸ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ አገሩ ፣ ሳባ ፣ የተባለው ፣ በሁለተኛው ፣ ሳባ ፣ በኢትዮጲስ ፣ አያት ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ በኢትዮጲስ ፣ ልጅ ፣ ሳባ ፣ አይደለም ። ይህም ፣ በዚሁ ፣ ዘመን ፣ አገሩ ፣ በስሙ ፣ ሳባ ፣ ይባል ፣ የነበረው ፣ የኢትዮጲስ ፣ አያት ፣ የነገደ ፣ አግዓዝያን ፣ መጀመሪያ ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፤ በበታቹ ፣ ወንድሞቹንና ፣ የወንድሞቹን ፣ ልጆች ፣ አንግሦ ፤ እርሱ ፣ በላይ ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ የሆነ ፣ ታላቅ ፣ ንጉሥ ፣ ነው ።

፮ ፤ በለው ፡ የአንሰባና ፡ የባርከ ፡ ወንዝ ፡ መረብም ፡ በሚወርድበት ፡ ከሳባ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ባለው ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ተቀመጠ ። አሁንም ፡ በደጭና ፡ (ሃርኪጎ ፡ )ያሉት ፡ ናይብች ፡ ከበለው ፡ የወረዱ ፡ ዘር ፡ ናቸው ፤ ባላባቶችም ፡ ናቸው ፤ ባላገሮቹም ፡ በለምች ፡ በሰገላና ፡ በሐማሴን ፡ ይቀመጣሉ ።

፯ ፤ በበለው ፡ ምድር ፡ የሚነገሩ ፡ ቋንቋዎች ፡ በደውኛ ፤ ትግሪኛ ፤ ህድ ፤ ዐረብኛ ፡ ናቸው ። በደውኛ ፡ ከግእዝና ፡ ከትግሪኛ ፡ ከዐረብኛም ፡ ጋር ፡ ይመሳሰላል ። ከዕብራይስጥም ፡ ጋር ፡ እንዲሁ ፡ በጣም ፡ ይመሳሰላል ። የበለው ፡ አገር ፡ እጅግ ፡ ባለከብትና ፡ ሰፊ ፡ የሆነ ፡ የአንድ ፡ ንጉሥ ፡ አገር ፡ ነበር ። ወሰኑ ፡ በምዕራብ ፡ አትባራ ፤ ወይም ፡ ተከዚ ፡ ነው ።

፰ ፤ ኖባ ፡ ምድሩ ፡ ከበለው ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ከአትባራ ፡ ወዲያ ፡ ነው ። ነጭ ፡ ዐባይና ፡ ጥቁር ፡ ዐባይ ፡ ከአገሩ ፡ ላይ ፡ ይፈስሳሉ ። የዚህ ፡ አገር ፡ ሕዝብና ፡ መንግሥት ፡ ኀይለኛ ፡ ነበርና ፡ ግብፆችን ፡ ያጠቃቸው ፡ ነበር ። አገሩም ፡ እጅግ ፡ ፍሬያም ፡ ነው ። እስላም ፡ ሳያሸንፋቸው ፡ አስቀድሞ ፡ የበለው ፡ መንግሥትና ፡ የኖባ ፡ መንግሥት ፡ ለሳባ ፡ መንግሥት ፡ የታወቁ ፡ ነበሩ ። ዛሬ ፡ ግን ፡ የኖባ ፡ መንግሥት ፡ እስላም ፡ ነው ።

፲ ፤ ከለው ፡ ከሳባ ፡ ወደ ፡ ምዕራብና ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ያለ ፡ የአማራ ፡ የወልቃይት ፡ የጠገዴ ፡ ሕዝብ ፡ አባት ፡ ነው ። የኢትዮጲስ ፡ ልጆች ፡ ፫ወንድማማቹ ፡ ነገድ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፤ በመልካቸውና ፡ በቁርበታቸው ፡ ከነዚህ ፡ ይመሳሰላሉ ። ከሌሎች ፡ ከአፍሪካ ፡ ሕዝብ ፡ ተለይተው ፡ በልዩ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ። እነዚህም ፡ ሕዝብ ፡ የያዙት ፡ አገር ፡ በጥቅሉ ፡ በአባታቸው ፡ ስም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

፲፩ ፤ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዋና ፡ ባላባቶች ፡ የሴም ፡ ዘሮች ፡ ፮ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። እነርሱም አማራ ፤ ትግሬ ፡ አገው ፤ በደው ፤ አስገዴ ፤ በቅላ ፤ ሐባብ ፡ ናቸው ። በደው ፡ አስገዴ ፡ በቅላ ፤ እኒህ ፡ ፫ቱ ፡ ነገድ ፡ በእስላም ፡ ሃይማኖት ፡ ገብተው ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ተለይተው ፡ ልዩ ፡ ወገኖች ፡ ሁነዋል ።

፲፪ ፤ አማራ ፤ ትግሬ ፤ አገው ፡ ግን ፡ በፊት ፡ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጊዜ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፤ በኋላም ፡ በክርስትና ፡ ያመኑ ፤ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ የጸኑ ፤ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ መንግሥት ፡ ያልጠፋባቸው ፤ ባዕድ ፤ ገዢ ፡ ያልገባባቸው ፤ የእግዚአብሔር ፡ ረድኤት ፡ ያልራቃቸው ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ።

፲፫ ፤ ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ አማሮችና ፡ ትግሮች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዋና ፡ ባላባቶችና ፡ ባላገሮች ፡ መሆናቸውንና ፡ ከሴም ፡ ዘር ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ልጆች ፡ የእስራኤል ፡ ዘሮች ፡ እንዲሆኑ ፡ የሚያስረዳ ፡ ብዙ ፡ ምስክር ፡ አላቸው ። እርሱም ፡ በ፲፩ ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል።

፲፬ ፤ መጀመሪያ ። ከሴም ፡ ዘር ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ እንደሆኑ ፡ የሚያስረዳ ፡ ከልዩ ፡ ወገን ፡ በመብልና ፡ በመጠጥ ፡ በመጋባትም ፡ አለመቀላቀላቸው ፡ ነው ። ሁለተኛ ፤ ስለነርሱ ፡ የሚናገር ፡ ታሪክ ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡ መገኘቱ ፡ ነው ። ሦስተኛ ፤ ስለ ፡ ኢት

ዮጵያ ፣ በመጽሐፍ ፣ ቅዱስ ፣ ትንቢት ፣ መነገሩ ፣ ነው ። አራተኛ ፣ አምልኮአቸው ፣ ነው ። አምስተኛ ፣ ግዝረታቸው ፣ ነው ። ስድስተኛ ፣ መልካቸው ፣ ነው ። ሰባተኛ ፣ ጠባያቸው ፣ ነው ። ስምንተኛ ፣ ቋንቋቸው ፣ ነው ። ዘጠኝኛ ፣ ስማቸው ፣ ነው ። ዐሥረኛ ፣ ስመ ፣ ሀገራቸው ፣ ነው ። ዐሥራ ፣ አንደኛ ፣ ልማደ ፣ ሀገራቸው ፣ ነው ።

፲፰ ፤ የነዚህን ፣ ያ፲፩ዱን ፣ ክፍሎች ፣ ምስክሮች ፣ ዋና ፣ አስረጂውን ፣ በዚህ ፣ እንዳን ጽፈው ፣ በየክፍሉ ፣ እጅግ ፣ ብዙ ፣ ነውና ፣ ነገር ፣ እንዳይበዛ ፣ በአጭሩ ፣ ትተነዋል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ነገደ ፣ ዮቅጣን ፣ የማን ፣ ልጆች ፣ ናቸው ? ፣ ትውልዳቸውን ፣ ዘርዝረህ ፣ ተናገር ።

፪ ፤ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የገቡት ፣ በየት ፣ ተሻግረው ፣ ነው ፣ ?

፫ ፤ ነገደ ፣ ዮቅጣን ፣ በየጊዜው ፣ ይጠሩባቸው ፣ የነበሩትን ፣ ፭ ፣ ስሞች ፣ ተናገር ።

፬ ፣ ኢትዮጲስ ፣ የነገሠው ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ዓመት ፣ ነው ፣ ?

፭ ፤ ኢትዮጲስ ፣ ከሞተ ፣ በኋላ ፣ የነገሠው ፣ ማነው ፣ ?

፮ ፤ የኢትዮጵያ ፣ ልጆች ፣ ማን ፣ ማን ፣ ይባላሉ ፣ ?

፲፩ ፤ ከኢትዮጵያ ፣ ሕዝብ ፣ ዋና ፣ ባላባቶች ፣ ማን ፣ ማን ፣ ናቸው ፣ ?

፲፪ ፣ አማሮችና ፣ ትግሮች ፣ የኢትዮጵያ ፣ ዋና ፣ ባላባቶችና ፣ ባላገሮች ፣ መሆናቸውን ፣ ደግሞም ፣ የሴም ፣ ዘር ፣ የነገደ ፣ ዮቅጣን ፣ ልጆች ፣ የእስራኤል ፣ ዘሮች ፣ መሆናቸውን ፣ የሚያስረዳ ፣ ምስክር ፣ አለህን ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፬ ።

### የትግሬ ፣ ሕዝብ ፣ ታሪክ ።

፩ ፤ በነገደ ፣ ኩሳ ፣ መንግሥት ፣ ጊዜ ፣ በዚያ ፣ ዘመን ፣ የህንድ ፣ ነገሥታት ፣ በር ትተው ፣ ወደ ፣ የመን ፣ እየመጡ ፣ ወጦር ፣ በዘረፋም ፣ ባወኩዋቸው ፣ ጊዜ ፣ በየ መን ፣ ከነበሩ ፣ ፭ቱ ፣ ነገደ ፣ ዮቅጣን ፣ ነገደ ፣ አቢማኤልና ፣ ነገደ ፣ ሀዊላ ፣ በዚ ያው ፣ በየመን ፣ ቀሩ ።

፪ ፤ ነገደ ፣ ሳባ ፤ ነገደ ፤ አባል ፣ ነገደ ፣ አፌር ፤ በነገደ ፣ ካም ፣ በኩሳ ፣ ዘር ፣ መንግ ሥት ፣ መጨረሻ ፣ ንጉሥ ፣ በጺኦሬ ፣ ፩ኛ ፣ ዘመን ፣ ከየመን ፣ ተነሥተው ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ መጡና ፣ ጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በአንድነት ፣ ተቀመጡ ። ከዚያ ፣ በኋላ ፣ ሦስቱ ፣ ወንድማማች ፣ ነገድ ፣ በምክር ፣ ተለያይተው ፣ አግዓዝያን ፣ የተባሉት ፣ ነገደ ፣ ሳባ ፣ በትግሬ ፤ ነገደ ፣ አባል ፣ በአዳል ፤ ነገደ ፣ አፌር ፣ በውጋዴን ፣ ተቀመጡ ።

፫ ፤ ነገደ ፣ ሳባ ፣ ነጋዶች ፣ ሆነው ፣ ለነገደ ፣ ኩሳ ፣ መንግሥት ፣ ቀረጥና ፣ ግብር ፣ በመስጠት ፣ ጥቂት ፣ ዘመን ፣ ስለ ፣ ተቀመጡበት ፣ የዚያን ፣ አገር ፣ ስም ፣ ትግሬ ፣

አሉት ። ትግሬ ፣ ማለት ፣ በቋንቋቸውና ፣ በዐረብኛ ፣ ነጋዴ ፣ ማለት ፣ ነው ። ከነዚህ ፣ ሕዝብ ፣ በላይ ፣ የኢትዮጲስ ፣ ፩ኛ ፣ ልጅ ፣ ሦስተኛ ፣ ሳባ ፣ በለጐልት ፣ ሆኖ ፣ ተሠርቶባቸዋል ።

፫ ፤ ትግሬ ፣ አግራ ፣ ማለት ፣ የግብር ፣ ስም ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ እንደ ፣ ሳባ ፣ እንደ ፣ ኖባ ፣ የተጸውዖ ፣ ስም ፣ አይደለም ። የትግሬ ፣ ሕዝብ ፣ በየጊዜው ፣ ፰ ፣ ስም ፣ ወጥቶለታል ፣ ሳባ ፣ በደው ፣ እረኞች ፣ ወይም ፣ ዘላን ፣ ትግሬ ፣ አግዓዚ ፣ ነው ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ነገደ ፡ ሳባ ፣ ነገደ ፣ አባል ፣ ነገደ ፣ አፌር ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የመጡት ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ?
ተለያይተው ፣ የሰፈሩባቸውን ፣ አገሮች ፣ ተናገር ።

፪ ፤ ትግሬ ፣ ማለት ፣ በቋንቋቸው ፤ ወይም ፣ በዐረብኛ ፣ ምን ፣ ማለት ፣ ነው ፣ ?

፫ ፤ ለትግሬ ፣ ሕዝብ ፣ በየጊዜው ፣ የወጡለትን ፣ ፰ ፣ ስሞች ፣ ተናገር ።

## ምዕራፍ ፣ ፺ ።

### ያማራ ፣ ሕዝብ ፣ ታሪክ ።

፩ ፤ ጨዋና ፣ ባለጌ ፣ ባላገር ፣ ልዩ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ተመልከት ። ባለጌ ፣ ባለርስት ፣ ባለመሬት ፣ ነው ። ጨዋ ፣ የንጉሥ ፣ አሽከር ፣ ነው ። እርሱም ፣ በባላገር ፣ ላይ ፣ የተሠራ ምሪተኛ ፣ ነው ። በዛሬ ፣ ቋንቋ ፣ ወታደር ፣ ይባላል ። ለዚህም ፣ ወታደር ፣ በየነገሠው ፣ ንጉሥ ፣ ዘመን ፣ በየአለቃው ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ የሆነ ፣ የጀግንነትና ፣ የክብረት ፣ ስም ያወጡለታል ። ደግሞ ፣ ያንዱን ፣ ነገድ ፣ ካንዱ ፣ ነገድ ፣ ለመደባለቅ ፣ ለነገሥታት ልማድ ፣ ስለ ፣ አላቸው ፣ ለወታደሮች ፣ መልከኝነት ፣ እያሉ ፣ ፩ ፣ ጭቃ ፣ ፪ ፣ ጭቃ ፣ ፫ ፣ ጭቃ ፣ እያደረጉ ፣ (እያሉ ፣)ይሰጡዋቸል ፤ ያም ፣ ወታደር ፣ በማያውቀው ፣ ሕዝብ ፣ ላይ ጨዋ ፣ ይሆናል ። ስለዚህ ፣ የመጣበት ፣ የማይታወቅ ፣ ብዙ ፣ ዐይነት ፣ ጨዋ ፣ በኢትዮጵያ ፣ ላይ ፣ ተሠርቶአል ።

፪ ፤ የአማራና ፣ የትግሬ ፣ አባት ፣ የሴም ፣ የልጁ ፣ ልጅ ፣ የኤቦር ፣ ልጅ ፣ ዮቅጣን ነው ። በመልክ ፤ በጠባይ ፤ በቋንቋ ፤ ጥቂት ፤ በጥቂት ፣ ይለያያሉ ፣ እንጂ ፣ ብዙ ፣ ነገር ፣ ይዋረሳሉ ። ደግሞም ፣ አማሮችና ፣ ትግሮች ፣ እንደ ፣ ነገደ ፣ እስራኤል ፣ ልጆች ፣ ሹልዳ ፣ ሥጋ ፣ አይበሉም ።

፫ ፤ ያማራ ፣ ሕዝብ ፣ የነገደ ፣ ሴም ፣ ወገኖች ፣ የዮቅጣን ፡ ልጆች ፣ የእስራኤል ፣ ዘሮች ፣ እንደ ፣ ሆኑ ፣ ፈጽሞ ፣ የሚያስረዳ ፣ ጠባያቸው ፤ ልማዳቸው ፤ መልካቸው ስማቸው ፤ ስመ ፣ ሀገራቸው ፤ ቋንቋቸው ፣ ነው ።

መንግሥቱ ፣ ያማራ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ አማርኛ ፣ ሠለጠነ ። ቋንቋቸውን ፣ እያጠፉ ፣ አማርኛ ፣ የሚናገሩ ፣ ብዙ ፣ ወገኖች ፣ አሉ ። እነዚህም ፣ ደምቢያዎች ፣ ቋሮች ፣ ጋፋቶች ፤ የወሎ ፣ ጋሎች ፤ የጆች ፣ ወይም ፣ ወረ ፣ ሴሆች ፣ ናቸው ። እንዲ

ሁም ፡ የወፍላ ፡ ሀሸንጌ ፡ ጋሎች ፡ ጋልኛን ፡ አጥፍተው ፡ ትግሪኛ ፡ ይናገራሉ ። ዳግመኛም ፡ አንድ ፡ ጨዋ ፡ መዳባይ ፡ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጊዜ ፡ የነበረ ፡ ነው ። በትግሬ ፣ በጠለምት ፣ በስሜን ፡ በወገራ ፡ የተሠራ ፡ ወታደር ፡ ነው ። ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የነገሡ ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ።

፬ ፣ ሦስተኛም ፡ በኋላ ፡ ባ፲፩፻፴ ፡ ወይም ፡ ፵ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በላሊበላ ፡ ንጉሥ ፡ ዘመን ፡ አማራ ፡ የተባለ ፡ ወታደር ፡ በዋድላ ፣ በበጌምድር ፣ በሳይንት ፣ በወለቃ ፡ ጨዋ ፡ ሆኖ ፡ በባላገሩ ፡ ላይ ፡ ተሠራበት ። ሳይንት ፡ ባላገሩ ፡ አረመኔ ፡ ነበረ ። መታመኛ ፡ ሲሉ ፡ ዘንዶውንና ፡ እባቡን ፡ ተመን ፡ አሉት ። ይህንኑ ፡ ሕዝብ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ያስተምሩት ፡ ነበሩ ። ፲፪ ፡ ዓመት ፡ በዚያ ፡ ወንጌልን ፡ ሲሰብኩ ፡ ካማሮች ፡ ጋር ፡ ተዋወቁ ። ከዛጔ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘር ፡ ቤተ ፡ መንግሥትን ፡ ለመመለስ ፡ የመከሩ ፡ በዚያ ፡ ነው ።

፭ ፣ አማሮች ፡ ጥንቱንም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ጋላ ፡ ወይም ፡ እስ ላም ፡ ክርስትና ፡ ሲነሣ ፡ አማራ ፡ ሆኑ ፡ ይባላል ።

፮ ፣ አምሓራ ፡ ወይም ፡ አማራ ፡ ማለት ፡ አራሽ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሳይንት ፡ ማለ ትም ፡ ባረብኛ ፡ የእኽል ፡ መከማቻ ፡ ጐተራ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፯ ፣ አማሮችም ፡ ይኩኖ ፡ አምላክን ፡ አንግሠው ፡ ከዛጔ ፡ ነገድ ፡ የሚሆን ፡ ንጉሥ ፡ ይትባረክን ፡ ዋድላ ፡ ላይ ፡ ገደሉት ። ካማራ ፡ ሕዝብ ፡ ነገርና ፡ ታሪክ ፡ መርማ ሪዎች ፡ ከኤውሮጳም ፡ የመጡ ፡ አማራ ፡ ከወዴት ፡ የመጣ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ ይጨነቃሉ ።

፰ ፣ አማራ ፡ ግን ፡ ከወዴትም ፡ አልመጣም ፣ ከያይነቱ ፡ የተጠራቀመ ፡ ኀይለኛ ፡ ግፈኛ ፡ አድመኛ ፣ ዕውቀት ፡ ያለው ፣ ጨካኝ ፡ ጭፍራና ፡ ጥሩ ፡ የላስታ ፡ ወታ ደር ፡ ነው ።

፱ ፣ ብዙ ፡ ዐዋቂዎች ፡ የሆኑ ፡ ታሪክ ፡ መርማሪዎች ፡ እንደ ፡ መሰላቸውና ፡ እንደ ፡ አገራቸው ፡ ልማድ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ጽፈዋል ፡ „ ንጉሥ ፡ ላሊበላን ፡ ወንድሙ ፡ ባሳደደው ፡ ጊዜ ፡ ምስር ፡ ወርዶ ፡ ከዚያ ፡ እስላም ፡ ያቅበዘበዛቸውን ፡ ፰ ፡ ሺ ፡ የሚ ሆኑ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሰብስቦ ፡ በዐባይ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ለዳር ፡ ይዞዋቸው ፡ ሲመጣ ፡ ነጭ ፡ ዐባይና ፡ ኒል ፡ ዐባይ ፡ በሚገናኙበት ፡ አጠገብ ፡ ውሃውን ፡ ወደ ፡ ሰሃራ ፡ ሊመ ልሰው ፡ አስቈፈረው ። ይህንንም ፡ ማድረጉ ፡ እስላሞች ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ በፈንታው ፡ እስላሞችን ፡ ለመበደል ፡ ነው ። ያም ፡ ስፍራ ፡ ዛሬ ፡ ክር ቱም ፡ ይባላል ። ክርቱም ፡ ማለት ፡ በትግርኛ ፡ ቊርጥ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ጐጃም ፡ ላይ ፡ ሰፈረ ። ይህንኑ ፡ ሠራዊት ፡ ይዞ ፡ ከወንድሙ ፡ ከአጼ ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ መንግሥትን ፡ ያዘና ፡ ሮሃ ፡ ገባ ። በሮሃ ፡ ያስወቀራቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ በነዚህ ፡ እጅ ፡ ነው ፡ ” ይላሉ ።

፲ ፣ እኛስ ፡ የሰማነው ፡ አባቶቻችንም ፡ የነገሩንና ፡ ከጥንት ፡ ጀምረው ፡ ያቈዩን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ ሳባ ፣ ኖባ ፣ በለው ፣ ከለው ፡ የተባሉ ፡ ኢትዮጵያን ፡

መግዛታቸውን ፡ ሀምያር ፡ የተባለ ፡ ዐረብ ፡ ሁሉን ፡ ጠቅልሎ ፡ መንገሡን ፡ ከነ ሱም ፡ የተሰበሰበው ፡ ወታደር ፡ ስለ ፡ አገልግሎቱ ፡ በባላገሩ ፡ ላይ ፡ ጩዋ ፡ ሆኖ ፡ መሠራቱን ፡ ነው ።

፲፩ ፤ አማሮች ፡ ግን ፡ ይኩኖ ፡ አምላክን ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አማርኛ ፡ ይናገር ፡ ጀመር ። ይኸውም ፡ አማርኛ ፡ ከአባቶቻችን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹና ፡ እንደ ፡ ጋሎች ፡ ከውጪ ፡ ሕዝብ ፡ የተወረሰ ፡ ቋንቋ ፡ አይደለም ። አማርኛ ፤ ከዕብራይስጥ ፤ ከግእዝ ፤ ከትግሪኛ ፤ ከዐረብ ፤ የመጣ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በምንም ፡ ምንም ፡ ከሌላ ፡ ቋንቋ ፡ የሚገናኝበት ፡ ቃል ፡ የለም ።

፲፪ ፤ ግእዝና ፡ ዐረብ ፤ ትግሪኛ ፤ በጣም ፡ ለማያውቅ ፡ ሰው ፡ አማርኛ ፡ ቢነግሩት ፡ አይሰማም ። ከቶውንም ፡ አማራው ፡ የአማራውን ፡ ቃል ፡ አይሰማውም ። ያመ ሰገነው ፡ መስሎ ፡ ቢረግመው ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ይሥቃል ።

፲፫ ፤ አዝማሪ ፡ በጥሩ ፡ አማርኛ ፡ ሲዘምር ፡ በላይ ፡ የሚሰማ ፡ አማርኛ ፡ አልብሶ ፡ በውስጥ ፡ ቢሳደብ ፤ ወይም ፡ ቢያከብርና ፡ ቢያመሰግን ፡ አማርኛን ፡ እጅግ ፡ አጥብቀው ፡ ካወቁት ፡ በቀር ፡ ሁሉ ፡ አያውቀውም ። የሚያስተውለው ፡ የለም ። ጕጃሜ ፡ ሲናገር ፤ ሼ ፡ ይቅርና ፡ በጌምድሬ ፡ አያውቀውም ። እገሌኮ ፡ እገሌን ፡ ባማርኛ ፡ ተናገረው ፡ ይባላል ። አማርኛ ፡ ማለት ፡ በፈረንጅ ፡ ቋንቋ ፡ ፖለ ቲካ ፡ ማለት ፡ ነው ። አማራም ፡ የኢትዮጲስ ፡ ልጅ ፡ ነው ። እርሱም ፡ በባላገር ፡ ላይ ፡ ጩዋ ፡ ሆኖ ፡ የተሠራ ፡ ሠራዊት ፡ ነው ።

፲፬ ፤ አማራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ እንዳይደለ ፤ ቋንቋውም ከአያቱ ፡ ከዕብራይስጥ ፤ ከአባቱ ፡ ከግእዝ ፡ ከወንድሞቹ ፡ ከዐረብና ፡ ከትግሬ ፡ የተ ወረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስረድተናል ። ባጼ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ጊዜ ፡ ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተጀመረ ፡ ማለት ፡ ፍጹም ፡ ጨዋታና ፡ ተረት ፡ ተርታ ፡ ነገር ፡ ነው ። ባጼ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ጊዜስ ፡ ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ፈጽሞ ፡ ሠለጠነ ። ያማረና ፡ የተወደደ ፡ ጕረሮ ፡ የማያንቅ ፡ ለንግግር ፡ የተስማማ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ቋንቋ ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ ንግግሩስ ፡ አስቀድሞ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ነው ።

፲፭ ፤ አጼ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ የነበሩና ፡ የነገሡ ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ በ፮ሺ ፡ ፯፻፶፫ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ በሺ ፡ ፪፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ነው ። ካጼ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ መጀመሪያ ፡ መንግሥት ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ. ም. ፮፻፹፫ ፡ ዓመት ፡ ነው ። አማ ርኛ ፡ ቋንቋ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ብቻ ፡ ተነገረ ፡ እንዳይባል ፤ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ከ፭ ሺ ፡ ፹፪ ፡ እስከ ፡ ፮ሺ ፡ ፬፻፴፫ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ካጼ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ በፊት ፡ ከሺ ፡ ፮፻፵ ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ አማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የሚያስረዳ ፡ ከዚህ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ የነገሡት ፡ የብዙዎች ፡ ነገሥታት ስም ፡ ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ መሆኑ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ማስረጃ ፡ ተገኝቶአል ።

፲፮ ፤ ይኸውም ፡ ወረደ ፡ ነጋሽ ፤ አግባ ፤ ጉም ፤ አስጕምጉም ፤ ለትም ፤ ተላተም ፤

ያደ ፤ ጎሽ ፤ አይዘር ፤ መራ ፣ ተክለ ፣ ሃይማኖት ፣ በመባላቸው ፣ ይታወቃል ። በፊት ፣ አማርኛ ፣ ቋንቋ ፣ ተሌለ፣ይህ ፣ ሁሉ ፣ ስም ፣ ከየት ፣ መጣ ፣ ?

፲፮ ፤ ደግሞም ፣ ከብዙ ፣ ዘመን ፣ በፊት ፣ የነበሩት ፣ ነገሥታት ፣ ስም ፣ የአማርኛ፣ ቋንቋ፣መሆኑ ፤ አማሮች ፣ በንጉሥ ፣ ላሊበላ ፣ ዘመን ፣ ከምስር ፣ የመጡ ፣ ናቸው፣ ብለው ፣ የጻፉትን ፣ ሰዎች ፣ አሳብ ፣ ያፈርስባቸዋል ። ያማራ ፣ ሕዝብ ፣ ከነገደ፣ ዮቅጣን ፣ ከኢትዮጲስ ፣ ልጆች ፣ (ዘር) እንደ ፣ ሆነ ፣ ገልጦ ፣ ያሳይባቸዋል ።

## ጥያቄ ፤

፩ ፤ ጨዋና ፣ ባለጌ ፣ ባላገር ፣ ማለት ፣ ምን ፣ ማለት ፣ ነው ፣ ?

፪ ፤ የአማራና ፣ የትግሬ ፣ አባት ፣ ማነው ፣ ?

፫ ፤ የራሳቸውን ፣ቋንቋ ፣ ረስተው ፣ በአማርኛ ፣ ወይም ፣ በትግርኛ ፣ የሚናገሩ ነገዶች ፣ ማንና ፣ ማን ፣ ናቸው ፣ ?

፬ ፤ የሳይንት ፣ ባላገር ፣ በምን ፣ ያመልክ ፣ ኑሮዋል ፣ ?

፭ ፤ አረመኔው ፣ ክርስቲያን ፣ ሲሆን ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ይበላል ፣ ?

፮ ፤ አምሓራ ፣ ወይም ፣ አማራ ፣ ማለት ፣ ምን ፣ ማለት ፣ ነው ፣ ? በዐረብኛ፣ ሳይንት ፣ ማለት ፣ ምን ማለት ፣ ነው ?

፯—፲፮ ፤ በትግሪኛ ፣ ክርቱም ፣ ማለት ፣ ምን ፣ ማለት ፣ ነው ፣ ? ስለ ፣ አማራ፣ ሕዝብና ፣ ቋንቋ ፣ ዘርዝረህ ፣ አስረዳ ።

## ምዕራፍ ፣ ፵፩ ።

### ስለ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ መምጣት ።

፩ ፤ በእስራኤል ፣ ንጉሥ ፣ በሰሎሞን ፣ ዘመን ፣ በመጽሐፍ ፣ ቅዱስ ፣ የሳባና ፣ የዓዜብ ፣ ንግሥት ፣ የተባለች ፣ የኢትዮጵያ ፣ ንግሥት ፣ ማክዳ ፣ የሰሎሞንን ፣ ጥበብ፣ ሰምታ ፤ እሱንና ፣ ጥበቡን ፣ ለማየት ፣ ከብዙ ፣ ጓዝ ፣ ጋር ፣ ወደ ፣ ኢየሩሳሌም፣ ወረደችና፣ ከሰሎሞን፣ቀዳማዊ ፣ ምኒልክን፣ፀንሳ ፣ ወደ ፣ አገርዋ ፣ ተመለሰች ። ከአገሩዋ ፣ ስትደርስ ፣ ስለ ፣ ተወለደ ፣ ስሙን ፣ የብልሀተኛ ፣ ልጅ ፣ ስትል ፣ እብነ፣ እል ፣ ኪም ፣ አለችው ። ከእናቱ ፣ ዘንድ ፣ አድጎ ፣ ፳፪፣ዓመት ፣ ሲሆነው ፣ አባቱን፣ ሰሎሞንን ፣ ለማየት ፣ ወደ፣ኢየሩሳሌም ፣ ወረደ ። በዚያ ፣ ሕገ ፣ኦሪትንንና ፣ ሕገ፣ መንግሥትን ፤ የዕብራይስጥን ፣ቋንቋ ፣ እየተማረ ፣ ፫ ዓመት ፣ ተቀመጠ ። ከዚህ፣ በኋላ ፣ አባቱ ፣ ንጉሥ ፣ ሰሎሞን ፤ ከ፲፪ቱ ፣ ነገደ ፣ እስራኤል ፣ ፲፪ ፣ ሺሕ ፣ የበኵር ፣ ልጆቻቸውን ፣ ብልሆችና ፣ ዐዋቂዎች ፣ የሆኑትን ፣ መርጦ ፤ ከተማሩት ፣ ክካህናትና ፣ ከመኳንንት ፣ ልጆች ፣ ፳፪ ፣ ታላላቅ ፣ አለቆች ፣ ሹሞ ፣ ልጁ፣ ምኒልክ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ንጉሥ ፣ ይሆን ፣ ዘንድ ፣ ልብሰ ፣ መንግሥት ፣ አሰፍቶ ፣ ቅብዐ ፣ መንግሥት ፣ በሊቀ ፣ ካህናቱ ፣ እጅ ፣ አስቀብቶ ፤ ሕገ ፣ ኦሪትን፣ሥርዓት፣

መንግሥትን ፡ ሰጥቶ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መልሶ ፡ ሰደደው ። እነዚህ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡት ፣ ባ፬ሺ፡፭፻፲፰ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ፱፻፹፪ ፡ ዓመት ፡ ከልደት ፡ በፊት ፡ ነው ።

፪ ፣ ንግሥት ፡ ማክዳን ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥትን ፡ ከአባትዋ ፡ ከተዋስያ ፡ ወርሳ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ እስከ ፡ የመን ፣ ከዚያም ፡ አልፋ ፡ እስከ ፡ ማደጋስካር ፡ የገዛች ፡ ንግሥት ፡ ናት ። ይኸንንም ፡ እኛ ፡ ብቻ ፡ ሳንሆን ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ሊቃውንትም ፡ መርምረው ፡ ተረድተው ፡ ጽፈዋል ።

፫ ፣ ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ የተባለ ፡ እንግሊዛዊ ፣ በታሪክ ፡ መጽሐፉ ፡ በ፪ኛው ፡ ክፍል ፡ በገጽ ፡ ፺፩ ፣ ስለ ፡ ንግሥት ፡ ማክዳ ፡ ሲናገር ፣ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በወንጌል ፡ እንዲያው ፡ በጭሩ ፡ ንግሥተ ፡ ዐዜብ ፡ ብሎ ፡ አነሣት ። የመጣችውም ፡ ከዓለም ፡ ዳርቻ ፡ ነው ፡ ይላል ፡ (ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፵፪ ፡ ) ከግዛትዋ ፡ የታወቀው ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ከአፍሪቃ ፡ ሰሜን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ማደጋስካር ፡ ድረስ ፡ ነው ። ዛሬ ግን ፡ ሳፍላ ፡ እንለዋለን ። ይህችም ፡ ንግሥት ፡ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ለማየት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ልትሄድ ፡ በተነሣች ፡ ጊዜ ፡ ሐበሾች ፣ የበርበር ፡ አሕዛብ ፡ ዐረቦች ፡ የሙር ፣ ሰዎች ፣ ተከተልዋት ። በዙሪያዋ ፡ ያለ ፡ አገር ፡ እርስዋን ፡ የማያመሰግን ፡ አልነበረም ፡ ይላል ።

፬ ፣ ሞሪዬ ፡ የተባለው ፡ የፈረንሳዊ ፡ ሊቅም ፡ ንግሥት ፡ ማክዳ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግሥት ፡ እንደሆነች ፡ ሲያስረዳ ፡ ንግሥት ፡ ማክዳ ፡ በአክሱም ፡ አጠገብ ፡ ባለች ፡ ሳባ ፡ በተባለች ፡ ከተማ ፡ ተቀበረች ። በመቃብሩዋም ፡ ላይ ፡ ፳፬ ፡ ሐውልቶች ፡ አሉበት ። አሁን ፡ ግን ፡ ተሰባብረዋል ፡ ይላል ። ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በጻፈው ፡ ታሪክ ፡ በሁለተኛ ፡ መጽሐፉ ፡ ፹፬ና ፡ ፹፭ ፡ እይ ።

፭ ፣ ዳግመኛም ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፣ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ በጻፈበት ፡ መጽሐፉ ፡ በ፪ኛው ፡ ክፍል ፡ በገጽ ፡ ፺፩ ፡ የሰሎሞንን ፡ ጥበብና ፡ ሥራውን ፡ ሰምታ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በአይሁድ ፡ ሃይማኖት ፡ ተጠመቀች ፣ ልጅም ፣ ወለደችለት ፡ ስሙም ፡ ምኒልክ ፡ ተባለ ፡ ይላል ።

፮ ፡ ሌሎችም ፡ እንደ ፡ አሚሮስ ፣ እንደ ፡ ሂሮዶቱስ ፡ ያሉ ፡ የግሪክ ፡ አገር ፡ ሊቃውንት ፣ እንደ ፡ መልዚ ፣ እንደ ፡ አኬሊ ፡ ዜዜኒ ፡ ያሉ ፡ የኢጣሊያ ፡ ሊቃውንት ፡ እንደነዚህም ፡ ያሉ ፡ ብዙዎች ፡ የኤውሮጳና ፡ የእስያ ፡ በጣም ፡ ታሪክ ፡ መርማሪዎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሴም ፡ ዘር ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ንግሥተ ፡ ዐዜብ ፡ ወይም ፡ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ከተማዋ ፡ በትግሬ ፡ ሳባ ፡ ይባል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ መርምረው ፡ ዐውቀው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግሥት ፡ መሆንዋንና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ እስከ ፡ የመን ፡ ከዚያም ፡ አልፋ ፡ እስከ ፡ ማዳጋስካር ፡ መግዛትዋን ፡ አስረድተው ፡ ጽፈዋል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ እስራኤል ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ?

፪ ፤ ንግሥት ፡ ማከዳ ፡ መንግሥትን ፡ የወረሰች ፡ ከማን ፡ ነው ፡ ?

፫ ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ስትሄድ ፡ የተከተሉዋት ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ ?

፬—፮ ፡ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግሥት ፡ መሆንዋንና ፡ የግዛትዋን ፡ ወሰን ፤ የኢትዮጵያም ፡ ሕዝብ ፡ የሴም ፡ ዘር ፡ መሆናቸውን ፡ መርምረው ፡ ዐውቀው ፡ የጻፉ ፡ የየት ፡ አገር ፡ ሊቃውንት ፡ ናቸው ፡ ? ስማቸውንና ፡ አገራቸውን ፡ ዘርዝረህ ፡ ተናገር ።

## ምዕራፍ ፡ ፺፪ ።

### ነገደ ፡ አገው ።

፩ ፤ ነገደ ፡ አገው ፡ በፊት ፡ ነገደ ፡ አዲል ፡ ይባሉ ፡ ነበሩ ። አዲል ፡ የዳዊት ፡ የልጁ ፡ ልጅ ፡ የይትርሃም ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ፪ ፡ ዜና ፡ መ ፡ ፫ ፡ እሱ ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጋር ፡ መጥቶ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲባል ፡ ከርሱ ፡ በታች ፡ የአገው ፤ የላስታ ፤ የገነት ፤ ( ዛሬ ፡ የጁ ፡ የተባለው ፤ ) በዙሪያው ፡ ላለው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ንጉሥ ፡ ሆነ ። የዳዊት ፡ የልጁ ፡ ልጅ ፡ የአምኖን ፡ ልጅ ፡ ኖን ፡ የተባለ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጋር ፡ መጥቶ ፡ ከርሱ ፡ በታች ፡ ሆኖ ፡ ከቋራ ፡ እስከ ፡ መተማ ፡ በታች ፡ ላለው ፡ አገር ፡ ንጉሥ ፡ ሆኖ ፡ ከተማ ፡ ውን ፡ በቋራ ፡ አደረገና ፡ አገሪቱንም ፡ ቋራ ፡ ብሎ ፡ ጠራት ። በቋራ ፡ የሚኖሩትም ፡ የርሱ ፡ ዘሮች ፡ በኖን ፡ ልጅ ፡ በሔት ፡ ስም ፡ ነገደ ፡ ሔት ፡ ተባሉ ። የጥንት ፡ ቋንቋቸው ፡ የተለየ ፡ ነበረ ። አሁን ፡ ግን ፡ የራሳቸውን ፡ ቋንቋ ፡ አጥፍተው ፡ በአማርኛ ፡ ይናገራሉ ። በጥንት ፡ ቋንቋቸው ፡ ኳራ ፡ ወይም ፡ ቋራ ፡ ማለት ፡ ፀሓይ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ቋንቋቸውም ፡ ከአገውኛ ፡ ጋር ፡ የተቀራረበ ፡ ነበር ፡ ይላሉ ።

፪ ፤ አገዎች ፡ ግን ፡ በሦስት ፡ ተከፍለው ፡ ቋንቋቸውም ፡ ሥሩ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ በየክፍላቸውና ፡ በየአገራቸው ፤ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ ሆነ ። እነርሱም ፡ በ፫ ፡ ስም ፡ ይጠራሉ ። የላስታ ፡ አገው ፤ የዳሞት ፡ አገው ፤ የሐሉል ፡ በጎለ ፡ አገው ፡ ይባላሉ ። የሁሉም ፡ መሠረትና ፡ ምንጭ ፡ የላስታ ፡ አገው ፡ ነው ።

፫ ፤ የዳሞት ፡ አገዎች ፡ ከላስታ ፡ አገው ፡ ተለይተው ፡ ሰባት ፡ ሆነው ፡ ዝሆንና ፡ ጎሽ ፡ አደን ፡ ብለው ፡ ሄዱ ። ያም ፡ አገር ፡ በዱር ፡ ያለው ፡ ዛፍ ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ንብ ፡ የበዛበትና ፡ ማር ፡ የሚገኝበት ፡ መልካም ፡ አገር ፡ መሆኑንና ፡ ሰው ፡ የሌለበት ፡ ጠፍ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተመልክተው ፡ ማርና ፡ የዱር ፡ እንስሳ ፡ ሥጋ ፡ እየበሉ ፡ ፯ ፡ ወር ፡ አገሩን ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ዞሩና ፡ መረመሩ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሚስቶቻቸውንና ፡ ልጆቻቸውን ፤ ላሞቻቸውንና ፡ ፍየሎቻቸውን ፡ ጓዛቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ወስደው ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ተቀመጡና ፡ አገሩን ፡ አቀኑ ። ባላገሮችና ፡ ባላባቶች ፡ ሆኑና ፡ አገሩም ፡ በስማቸው ፡ አገው ፡ ምድር ፡ ተባለ ። በ፯ቱ ፡ አባቶችም ፡ በየ

ክፍሉ ፡ ሲዘረዘር ፡ ፯ ፡ ቤት ፡ አገው ፡ ይባላል ። በ፯ቱ ፡ አባቶቻቸው ፡ ስም ፡ አገራቸውን ፡ ሰይመው ፡ ፯ ፡ ቤት ፡ አገው ፡ ተብለው ፡ በየአገራቸውና ፡ በየክፍላቸው ፡ ይጠራሉ ።

፬ ፤ የሀልሀል ፡ በጎሰ ፡ አገዎች ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ዘመን ፡ በያገሩ ፡ ረኃብ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ እንዲሁ ፡ ከላስታ ፡ አገው ፡ ተለይተው ፡ ፯ ፡ ወንድማማቾች ፡ ከነሚስቶቻቸውና ፡ ከነልጆቻቸው ፤ ፫—እኅቶቻቸውም ፡ ከነባሎቻቸው ፡ ተሰደው ፡ ሀልሀል ፡ በጎሰ ፡ ገቡ ። በዚያም ፡ ዱሩን ፡ መንጥረው ፤ እባቡን ፡ ፈጅተው ፤ ቤት ፡ ሠርተው ፤ አገር ፡ አቅንተው ፡ ተቀመጡ ፡ ይባላል ።

፭ ፤ የላስታ ፡ አገዎች ፡ በዋግ ፡ የሚኖሩ ፡ ዋኖቹ ፡ እነርሱ ፡ ናቸውና ፡ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጊዜ ፡ የያዙትን ፡ አገር ፡ ሳይለቁ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ያሉት ፡ በዚያው ፡ ነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ነገደ ፡ አገው ፡ አስቀድሞ ፡ ማን ፡ ይባሉ ፡ ኑረዋል ፡ ? አዲል ፡ የማን ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ? ኖንስ ፡ ? ሔትስ ፡ ?

፪ ፤ ነገደ ፡ አገው ፡ ስንት ፡ ክፍል ፡ ናቸው ፡ ? የሚጠሩበትን ፡ ስም ፡ ዘርዝረህ ፡ ተናገር ።

፫ ፤ አገዎች ፡ ከላስታ ፡ ተነሥተው ፡ የሄዱት ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፺፫ ።

### ነገደ ፡ አስማክህ ።

፩ ፤ ነገደ ፡ አስማክህ ፤ ከምስር ፡ ንጉሥ ፡ ከጥሳሜቲክ ፡ ፩ኛ ፡ ፈርዖን ፡ ስለ ፡ ተጣሉ ፤ ባ፬፻ ፡ ፳፻፸፫ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ በ፯፻፳፯ ፡ ዓመት ፡ ከልደት ፡ በፊት ፡ ፪፻፵፻ ፡ ሠራዊት ፡ ሁነው ፡ ከድተው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጡና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ለዊያንኪሂ ፡ ፬ኛ ፡ ገቡለት ። እርሱም ፡ በናዋታን ፡ ሳለ ፡ ያላሰባቸውን ፡ ረዳቶች ፡ በድንገት ፡ ስለ ፡ አገኘ ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተቀበላቸው ። ከደስታውም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ፈጥኖ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ አገር ፡ ሰጣቸው ። ደግሞም ፡ ጠላቶቹ ፡ ይዘውት ፡ የነበረውን ፡ ምዕራባዊ ፡ አገር ፡ እንዲያቀኑለት ፡ አሎ ፡ ፈቀደላቸው ። ያለ ፡ ጥርጥር ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሕዝብ ፡ በአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መንበሩን ፡ ትቶ ፡ ነበረ ። ነገደ ፡ አስማክህ ፡ እንዲህ ፡ ሁነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቀሩ ። በፊት ፡ በሰናሒት ፡ ነበሩ ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ነጭ ፡ ዐባይና ፡ ጥቍር ፡ ዐባይ ፡ በሚገናኙባቸው ፡ ወንዞች ፡ መኻከል ፡ ተቀመጡ ፤ ታላቅ ፡ ሕዝብም ፡ ሆኑ ፤ የነሱ ፡ ወገኖች ፡ ከ፫፻ ፡ ዓመት ፡ የሚበልጥ ፡ የያዙትን ፡ ኤዛር ፡ የተባለውን ፡ ከተማ ፡ ሠሩ ። ብዙ ፡ የምስርን ፡ ልማድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አስተማሩ ። የእሎም ፡

መንግሥት ፡ ዛሬ ፡ ሴዮክ ፡ ለተባሉት ፡ አለፈ ። በአስትራቦን ፡ ዘመን ፡ አንዲት ፡ መንግሥት ፡ ነበረች ። በጵሊን ፡ ጊዜያት ፡ ያቆሙት ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ እንዳ ልነበረ ፡ ሆነ ።

፪ ፤ ይህም ፡ የ፪፻፵ሺ ፡ ሠራዊት ፡ ክዳት ፡ ያገሩ ፡ ዋና ፡ ሠራዊት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የም ስርን ፡ መንግሥት ፡ እጅግ ፡ ጎዳውና ፡ አደከመው ። የውጪ ፡ ሰዎች ፡ በዘመ ቱበት ፡ ጊዜ ፡ ሊቃወም ፡ ስላልቻለ ፡ የፒርስ ፡ ሰዎች ፡ ምስርን ፡ በዘንግ ፡ ሊገዙት ፡ ሆነ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ነገደ ፡ አስማክህ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ቍጥራቸው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ፡ ?
እነዚሁ ፡ ሕዝብ ፡ ዜጋ ፡ የሆኑለት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ?
፪ ፤ ነገደ ፡ አስማክህ ፡ ስለ ፡ ከዱት ፡ በምስር ፡ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ደረሰበት ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፺፬ ።

### ነገደ ፡ ፈላሻ ።

፩ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ያሉ ፡ ፈላሻ ፡ ሕዝብ ፡ ሥራቸውና ፡ ምንጫቸው ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ የእስ ራኤል ፡ ዘር ፡ ናቸው ፡ ከጳለስቲና ፡ ከእስራኤል ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጡት ፡ ግን ፡ በየዘመኑ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

፪ ፤ መጀመሪያ ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጋር ፡ ከመጡት ፡ ከእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ መጥተው ፡ እስከ ፡ ዘመነ ፡ ወንጌል ፡ አንድነት ፡ የተቀመጡ ፡ ናቸው ። በአባ ፡ ሰላማ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብና ፡ ነገሥታት ፤ የመንግሥትም ፡ ዘር ፡ ሁሉ ፡ በወንጌል ፡ አምነው ፡ ክርስቲያን ፡ ሲሆኑ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ከወንድሞ ቻቸውና ፡ ከወገኖቻቸው ፡ ተለይተው ፡ በወንጌል ፡ አናምንም ፡ ክርስቲያን ፡ አንሆ ንም ፤ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ አንለቅም ፡ ብለው ፡ ተለይተው ፡ የቀሩ ፡ ናቸው ።

፫ ፤ ሁለተኛ ፡ የሮም ፡ ነገሥታት ፡ አስብያኖስና ፡ ጥጦስ ፤ ኢየሩሳሌምን ፡ አፍርሰው ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ አቃጥለው ፡ እስራኤልን ፡ በፈጁዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ከሞት ፡ የተረፉ ፡ እስራኤል ፡ በያገሩ ፡ ሲበታተኑ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ከጳለስቲና ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገቡ ።

፬ ፤ ሦስተኛ ፡ በዮዲት ፡ (ጉዲት) ዘመን ፡ ከምስር ፡ ንጉሥ ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ ኢት ዮጵያ ፡ ገብተው ፡ ከፊተኞቹ ፡ ፈላሾች ፡ ጋር ፡ ተቀላቀሉ ። ፈላስያን ፡ ማለት ፡ ስደ ተኞች ፡ ማለት ፡ ነው ። በዘመን ፡ ብዛት ፡ ፈላሻ ፡ ተባሉ ። እነዚሁ ፡ ሕዝብ ፡ በያ ገሩ ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ አሉ ። የሚበዙት ፡ ግን ፡ በጭልጋ ፤ በጋባ ፤ በአርማጭሆ ፤ በወልቃይት ፤ በጠገዴ ፡ በቈላ ፡ ወገራ ፤ በጎንደር ፡ ከተማ ፡ ዙሪያ ፡ ይኖራሉ ።

፰ ፤ ደግሞም ፡ በአጼ ፡ ካሌብ ፡ ዘመን ፡ ዙዋኑስ ፡ ወይም ፡ ፊንሐስ ፡ የተባለ ፡ አይሁዳዊ ፡ በየመን ፡ ክፍል ፡ ያለችውን ፡ ሀገረ ፡ ናግራንን ፡ አጥፍቶ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ አቃጥሎ ፡ ክርስቲያናቱንም ፡ በፈጀ ፡ ጊዜ ፡ አጼ ፡ ካሌብ ፡ ሄደው ፡ ይህን ፡ ዙዋኑስ ፡ ወይም ፡ ፊኒሐስ ፡ የተባለውን ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ገድለው ፤ ከርሱ ፡ ጋር ፡ የተባበሩትን ፡ አይሁድ ፤ ስለ ፡ ፈጁዋቸው ፤ ከሞት ፡ ያመለጡት ፡ አይሁድ ፡ ወይም ፡ ፈላሾች ፡ በባል ፡ እልመንደብ ፡ ተሻግረው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከሚኖሩ ፡ ፈላሾች ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ጋር ፡ ተቀላቀሉ ፡ የሚሉም ፤ አሉ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ነገደ ፡ ፈላሻ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡት ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
፪ ፤ ሃይማኖታቸው ፡ ምንድነው ፡ ?
፫ ፤ ነገደ ፡ ፈላሻ ፡ መኖሪያቸው ፡ በየት ፡ ክፍል ፡ ነው ? ፤

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፶፰ ።

### ነገደ ፡ ጋፋት ።

፩ ፤ ነገደ ፡ ጋፋት ፡ ሁለት ፡ ወገንና ፡ ክፍል ፡ ናቸው ። መጀመሪያ ፡ የኩሳ ፡ ወገን ፡ ጋፋት ፡ ሁለተኛ ፡ የእስራኤል ፡ ወገን ፡ ጋፋት ፡ ይባሉ ፡ ነበሩ ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በጋብቻና ፡ በንብረት ፡ ተቀላቀሉና ፡ አንድ ፡ ጋፋት ፡ ተባሉ ።

፪ ፡ የኩሳ ፡ ጋፋት ፡ አባት ፡ ስሙ ፡ ጋፋት ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ተካም ፡ ልጅ ፡ ከኩሳ ፡ ዘር ፡ ነበር ። ነገደ ፡ ኩሳ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ለቀቀው ፡ አግዓዝያን ፡ የተባሉ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ የኢትዮጵያን ፡ አገርና ፡ መንግሥት ፡ በያዙ ፡ ጊዜ ፤ ይህ ፡ ጋፋት ፡ ከነልጆቹ ፡ ያዘዛችሁትን ፡ ሠርቼ ፡ ለናንተ ፡ ተገዝቼ ፡ እኖራለሁ ፤ ወደማላውቀው ፡ አገር ፡ አልሰደድ ፡ በለመድኩት ፡ልኑር ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ላከ ። እነርሱም ፡ ያዘዝንህን ፡ ሠርተህ ፡ ለኛ ፡ ተገዝተህ ፡ ከኖርህ ፡ ምረንሃል ፡ ግባ ፡ ስለ ፡ አሉት ፡ መጥቶ ፡ ከነልጆቹ ፤ ገባና ፡ ያዘዙትን ፡ ከነልጆቹ ፡ እየሠራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ዜጋ ፡ ሆኖ ፡ ተቀመጠ ።

፫ ፤ የእስራኤል ፤ ወገን ፡ ጋፋት ፡ የተባሉ ፤ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከሮብዓም ፡ ከሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ ከወንድሙ ፡ በክፋቱ ፡ ሸፍተው ፡ ተዋጉትና ፡ ድል ፡ ስለሆኑ ፡ አግኝቶ ፡ እንዳያጠፋቸው ፡ ፈርተው ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፤ መጡና ፡ በዳሞት ፡ ሰፈሩ ። ጋፋት ፡ ማለትም ፡ ስደተኛ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፬ ፤ በፊት ፡ እንዳልነው ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ወገን ፡ ጋፋት ፤ በጋብቻ ፡ በግብር ፤ በሥርዓት ፡ ተቀላቀሉና ፡ ባንድ ፡ ስም ፡ ጋፋት ፡ ተባሉ ። ጋፋቶች ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ትውልዳቸው ፡ ቢጠይቁዋቸው ፡ ከምን ፡ ዘር ፡ እንደሆኑ ፡ አያውቁምና ፡ የኛ ፡ አባት ፡ የመጣው ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጽላተ ፡ሙሴን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ይዞ ፡ የመጣ ፡ ጊዜ ፡

ነው ። ከጕዞ ፣ ላይ ፣ ከጠባብ ፣ ስፍራ ፣ ላይ ፣ አልፋለሁ ፣ ሲል ፣ ታቦቷቱን ፣ ገፋት ፣ ገፋት ፣ እያሉ ፣ ተቈጡ ። በዚህ ፣ ምክንያት ፣ አባታችን ፣ ስሙ ፣ ጋፋት ፣ ተባለ ፣ ብለው ፣ ብቻ ፣ ይተርካሉ ፤ የተጻፈ ፣ ግን ፣ የለም ። ይህ ፣ ከሆነ ፣ የፊተኛው ፣ ስሙ ፣ ማን ፣ ነበረ ፣ ቢሉዋቸው ፣ ምንም ፣ ሊመልሱ ፣ አይችሉም ።

፭ ፤ ጋፋት ፣ ዐሥር ፣ ወንዶች ፣ ልጆች ፣ ወለደ ፤ ስማቸውም ፣ ይህ ፣ ነው ። አብድራይ ፤ ገምቦ ፤ ቢረባቦ ፤ የዘምበል ፣ የሱብሊ ፤ አሽመን ፤ ሀርበዋሽ ፤ ሀርብ ፣ አክል ፤ ወንጌ ፤ ድን ፤ እነዚህም ፣ የጋፋት ፣ ልጆች ፤ በየልጆቻቸውና ፣ በየወገናቸው ፣ ደግሞ ፣ በ፲ ፣ ነገድ ፣ ተከፍለው ፣ በውስጥ ፣ በየአባቶቻቸው ፣ ስም ፣ ይጠራሉ ። በላይ ፣ ግን ፣ ነገደ ፣ ጋፋት ፣ በመባል ፣ ባያታቸው ፣ ስም ፣ በአንድ ፣ ተጠቅልለው ፣ ይጠራሉ ።

፮ ፤ የአብድራይ ፣ ልጆች ፣ ነገደ ፣ አብድራይ ፣ ይባላሉ ፣ ሁሉም ፣ እንዲሁ ፣ በየአባቶቻቸው ፣ ስም ፣ ነገደ ፣ ገምቦ ፤ ነገደ ፣ ቢረባቦ ፣ ነገደ ፣ የዘምበል ፣ ነገደ ፣ የሱብሊ ፣ ነገደ ፣ አሽመን ፤ ነገደ ፣ ሐርበዋሽ ፤ ነገደ ፣ ሀርብ ፣ አክል ፤ ነገደ ፣ ወንጌ ፤ ነገደ ፣ ድን ፣ ይባላሉ ።

፯ ፣ እነዚህም ፣ ሕዝብ ፣ ከብዙ ፣ ዘመን ፣ በኋላ ፣ ቀማኞች ፤ ሌቦች ፤ ግፈኞች ፣ ሆኑ ። ስለዚህ ፣ ነገሥታት ፣ በየዘመናቸው ፣ ይዘርፋዋቸውና ፣ ያጠፋዋቸው ፣ ነበር ።

፰ ፤ ነገደ ፣ ጋፋት ፣ በፊት ፣ በሸዋ ፣ ይኖሩ ፣ ነበር ፤ በኋላ ፣ ግን ፣ ከሸዋ ፣ ፈልሰው ፣ ጐጃም ፣ ተሻገሩ ። የሚበዙት ፣ ቈላውን ፣ የዐባይን ፣ ዳር ፣ ተከትለው ፣ እስከ ፣ ድን ፣ በዳሞት ፣ ይኖራሉ ። በሸዋ ፣ በበጌምድርም ፣ ጥቂት ፣ ጥቂት ፣ አሉ ። ደግሞም ፣ በደብረ ፣ ታቦር ፣ አጠገብ ፣ የነበሩበት ፣ ሰላምኮ ፣ የተባለው ፣ አገር ፣ እስካሁን ፣ በስማቸው ፣ ጋፋት ፣ ይባላል ። በእስቴም ፣ መካነ ፣ ኢየሱስ ፣ አጠገብ ፣ ያሉበት ፣ አገር ፣ በስማቸው ፣ ጋፋቶች ፣ ይባላል ። በሸዋም ፣ በደብረ ፣ ሊባኖስና ፣ በጅር ፣ መኻከል ፣ በል ፣ ጋፋት ፣ ይባላል ።

፱ ፤ ነገደ ጋፋት ፣ ጥንት ፣ አረማውያን ፣ ነበሩ ። አሁን ፣ ግን ፣ ክርስቲያኖች ፣ ናቸው ። በአማራ ፣ ሕዝብ ፣ መኻከል ፣ ስለ ፣ ተቀመጡ ፣ ቋንቋቸውን ፣ አጥፍተው ፣ በአማርኛ ፣ ይናገራሉ ። አንዳንዶቹ ፣ የጥንት ፣ ቋንቋቸውን ፣ ያልረሱት ፣ የምሥጢር ፣ ነገር ፣ ብቻ ፣ ሲሆን ፣ በጥንት ፣ ቋንቋቸው ፣ ይናገራሉ ፣ እንጂ ፣ ዋና ፣ ቋንቋ ፣ አድርገው ፣ አይነጋገሩበትም ፤ ዋና ፡ ቋንቋቸው ፣ ግን ፣ አማርኛ ፣ ነው ።

ፈላሻና ፣ ጋፋት ፣ ዛሬ ፣ ክርስቲያን ፣ ሆነው ፣ በክርስቲያን ፣ መኻከል ፣ ሲኖሩ ፣ ሥራቸው ፣ ሸማ ፤ ብረት ፤ ቁርበት ፤ መሰንቆ ፣ መምታት ፤ አዝማሪዎች ፤ ሀሚናዎች ፤ ሌላም ፣ የእጅ ፣ ሥራ ፣ የሚያውቁ ፣ ናቸው ።

## ጥ ያ ቄ ፤

፩ ፤ ነገደ ፣ ጋፋት ፣ ስንት ፣ ክፍል ናቸው ፣ ?

፪ ፤ ነገደ ፣ ጋፋት ፣ የማን ፣ ዘር ፣ ናቸው ፣ ?

፫ ፤ ጋፋት ፣ ማለት ፣ ምን ፣ ማለት ፣ ነው ፣ ? መኖሪያቸው ፣ በየት ፣ ክፍል ፣ ነው ፣ ?

፬ ፡ የጋፋትን ፡ ልጆች ፡ ስምና ፡ የሚኖሩበትን ፡ ክፍል ፡ ሃይማኖታቸውንና ፡ ቋንቋቸውን ፡ ግብራቸውንና ፡ ሥራቸውን ፡ ዘርዝረህ ፡ ተናገር ።

## ምዕራፍ ፡ ፺፮ ።

### ነገደ ጋላ ።

፩ ፤ እነዚህ ፡ የጋላ ፡ ሕዝብ ፡ ከእስያ ፡ ፈልሰው ፡ ወደ ፡ ማዳጋስካር ፡ ተሻገሩ ፡ ከዚያም ፡ ፈልሰው ፡ በባሳ ፡ አጠገብ ፡ ካለው ፡ የባሕር ፡ ወደብ ፡ ተቀመጡ ። በጋልኛ ፡ በባሳ ፡ ማለት ፡ ለሰውም ፡ ለከብትም ፡ መሰማርያ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከዚያም ፡ ገናሌ ፡ የተባለውን ፡ ወንዝ ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወጡ ፤ ከገራቸው ፡ ሲወጡ ፡ ግን ፡ የወደደው ፡ ወጥቶ ፡ ያልወደደው ፡ ቀረ ፡ እንጂ ፡ ሁሉም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አልወጡም ።

፪ ፤ ይህ ፡ ጋላ ፡ የተባለ ፡ ሕዝብ ፡ ከዚያ ፡ ተነሥቶ ፡ መጣና ፡ በባሌ ፡ ዳር ፡ ገላና ፡ በሚሉት ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጦ ፡ ላሙንና ፡ ፍየሉን ፡ በጉን ፡ እያረባ ፡ እንደ ፡ ዘላን ፡ ሆኖ ፡ ኖረ ። የመጣበትም ፡ ጊዜ ፡ ከአጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ (ስመ መንግሥታቸው ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ) ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በፊት ፡ ፻፪ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ይህም ፡ አጼ ፡ ይስሐቅ ፡ በነገሡ ፡ በ፰ ፡ ዓመት ፡ በ፮ሺ ፡ ፱፻፬ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ባ፲፬፻፬ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ አሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ እውነተኛው ፡ የጋሎች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መውጣት ፡ መራ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ (ስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ዛጌ) ፡ በነገሠ ፡ ባ፲ ፡ ዓመት ፡ በ፱፻፴ ዓ. ም. ነው ።

፫ ፤ ጋሎች ፡ በገናሌ ፡ ወንዝ ፡ መጥተው ፡ ሆር ፡ ውላቦ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ገቡ ። በሆር ፡ ውላቦ ፡ ዋናተኛ ፡ በዋና ፡ የሚቈርጣትና ፡ የሚሻገራት ፡ ትንሽ ፡ ኩሬ ፡ (ባሕር) ፡ አለች ። ጋሎች ፡ የተፈጠርነው ፡ ከዚህ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ስለዚህ ፡ ዑሜን ፡ ውላቦ ፡ ባቴ ይላሉ ። ይህም ፡ ፍጥረት ፡ ከውላቦ ፡ ውሃ ፡ ወይም ፡ ባሕር ፡ ወጣ ፡ ማለት ፡ ነው ። ጋሎች ፡ ለውሃ ፡ የሚሰግዱት ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። ሰውም ፡ እንስሳም ፡ ከዚያ ፡ ውሃ ፡ አይጠጣም ፡ ክልክል ፡ ነው ። ጋላ ፡ ሁሉ ፡ ከዚያ ፡ ብዙ ፡ ሠንጋና ፡ ፍሪዳ ፡ በግና ፡ ፍየል ፡ ሁሉ ፤ ያርዳሉ ። ለውሃውም ፡ ይሰግዳሉ ። በሆር ፡ ውላቦ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ ያላቸው ፡ ጥቂት ፡ ሕዝብ ፡ አሉ ። ደራስ ፡ ይባላሉ ። የጋላን ፡ ሕዝብ ፡ ይመስላሉ ። ከሲዳሞ ፡ እስከ ፡ ውላቦ ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ከውላቦ ፡ እስከ ፡ ቦረን ፡ ፰ ፡ ቀን ፤ ያስኬዳል ።

፬ ፤ ጋሎች ፡ ሁለት ፡ ነገድ ፡ ናቸው ። በርቱማ ፡ ቦረን ፡ ይባላሉ ። ወንድማማች ፡ ናቸው ። በርቱማ ፡ ፯ ፡ ቦረን ፡ ፲፩ ፡ ሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ ፲፯ ፡ ልጆች ፡ ወለዱ ። የበርቱማ ፡ ልጆች ፡ ከረዩ ፡ መረዋ ፡ ኢቱ ፡ አክቹ ፡ ወረነሻ ፡ ሁበና ፡ ናቸው ። የከረዩ ፡ ልጆች ፡ ሊበን ፤ ሜጫ ፤ ቱለማ ፤ ወሎ ፤ ጅሌ ፤ ኢቦ ፤ ሉባ ፤ በላእ ፡ ናቸው ። የመረዋ ፡ ልጆች ፤ ወርድያን ፤ አሩሲ ፤ ኢቱ ፤ ጥሙጋ ፤ ናቸው ።

የወርድያን ፡ ልጆች ፤ አና ፤ ኡር ፤ አበጢ ፤ ናቸው ። እኒህ ፡ ሁሉ ፡ የመረዋ ፡ ልጆች ፡ በኃይልና ፡ በብዛት ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጣሉ ። የኢቱ ፡ ልጆች ፡ ጅሌ ፤ ሲባ ፡ ናቸው ። የአከቹ ፡ ልጆች ፡ ጅንጉር ፡ ጩፋ ፡ ናቸው ። የወረነሳ ፡ ልጆች ፤ ሶዶ ፡ አቡ ፤ ጫቡ ፤ ይሉ ፤ ጉድሩ ፤ ኩታይ ፤ አምሩ ፤ ሁሮ ፤ ናቸው ። የሁበና ፡ ልጆች ፤ ራያ ፤ አዘቦ ፤ አሸንጌ ፡ ናቸው ። ከነዚህ ፡ የሚጫ ፡ ልጆችና ፡ ከጋላ ፡ ቤት ፡ ሚጫ ፡ ታላላቆቹ ፡ ተነሥተው ፤ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ለአጼ ፡ ዐምደ ፡ ጽዮን ፡ አደሩ ፡ እር ሱም ፡ በመልካም ፡ ተቀብሎ ፡ በጣና ፡ በሕርና ፡ በዳሞት ፡ መኻከል ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ስለ ሰጣቸው ፡ ያንን ፡ አገር ፡ ተቀብለው ፤ ያዙና ፡ በአባታቸው ፡ ስም ፡ ሚጫ ፡ አሉት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ክርስትና ፡ ተነሥተው ፡ በተቀበሉት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስ ቲያናትን ፡ ሠርተው ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁነው ፡ ተቀመጡ ። ከአማራም ፡ ሕዝብ ፡ መኻ ከል ፡ ጋልኛን ፡ ፈጽመው ፡ አጥፍተው ፡ በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ብቻ ፡ ይናገራሉ ።

፭ ፤ የወሎ ፡ ልጆችም ፡ የያዙት ፡ አገር ፡ በአማራ ፡ ሕዝብ ፡ መኻከል ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ጋል ኛን ፡ አጥፍተው ፡ በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ይናገራሉ ። ጥንት ፡ ክርስቲያን ፡ ሁነው ፡ አት ሮንስ ፡ ማርያም ፤ መካነ ፡ ሥላሴ ፤ ደብረ ፡ ገነት ፡ ገነተ ፤ ጊዮርጊስ ፡ እኒህን ፡ የመ ሰሉ ፡ አድባራትና ፡ ብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ነበሩባቸው ። አገሩ ፡ ጥንት ፡ ላኮ ፡ መልዛ ፡ ይባል ፡ ነበር ፤ የወሎ ፡ ልጆች ፡ ከያዙት ፡ በኋላ ፡ ግን ፤ የአገሩን ፡ ስም ፡ ለውጠው ፡ በአባታቸው ፡ ስም ፡ ወሎ ፡ አሉት ። ግራኝ ፡ በአገራቸው ፡ ውስጥ ፡ የነ በሩትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አጥፍቶና ፡ አቃጥሎ ፡ መጻሕፍትን ፡ ቈነጻጽሎ ፡ ባጠፋባቸው ፡ ጊዜ ፡ የሐረርጌ ፡ እስላሞችና ፡ ፋቅሮች ፡ ገብተው ፡ የሙሐመድን ፡ ሃይማኖት ፡ በቍርዓን ፡ ስላስተማሩዋቸው ፡ የወሎ ፡ ሰዎች ፡ ፈጽመው ፡ ሰለሙ ። አሁን ፡ ግን ፡ ብዙዎቹ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያንነታቸው ፡ ተመልሰዋል ።

፮ ፤ ከሁበና ፡ ልጆችም ፡ ሀሸንጌ ፡ የትግሬ ፡ ጐረቤት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከራያና ፡ ከአዘቦ ፡ ተለ ይቶ ፡ ክርስቲያን ፡ ነው ። በልማድና ፡ በግብር ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ እንደ ፡ ራያና ፡ እንደ ፡ አዘቦ ፡ ናቸው ። የሐሸንጌ ፡ ጋሎች ፡ ጋልኛን ፡ አጥፍተው ፡ በትግሪኛ ፡ ይናገራሉ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ነገደ ፡ ጋላ ፡ ወደ ፡ መኻል ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
፪ ፤ ጋሎች ፡ ለውሃ ፡ የሚሰግዱበት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ?
፫ ፤ ጋሎች ፡ ስንት ፡ ነገድ ፡ ናቸው ፡ ? ትውልዳቸውን ፡ ዘርዝረህ ፡ ተናገር ።
፬ ፤ የወሎ ፡ ሕዝብ ፡ የያዙት ፡ አገር ፡ በየትኛው ፡ ሕዝብ ፡ መኻከል ፡ ነው ፡ ? ቋንቋቸው ፡ የምንድነው ፡ ? ሃይማኖታቸው ፡ ጥንት ፡ ምን ፡ ኑሮዋል ፡ ? ያሰለማቸው ፡ ማነው ፡ ?